# ታጠቅ

አለም አቀፍ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር
የቴዎሪ መፅሄት

በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር የተዘጋጀ

## የብሔሮች ጉዳይ

የመፅሄት አዘጋጅ ቦርድ፡
P.O.BOX 3198
103 64 STOCKHOLM 3
SWEDEN

ቁጥር፡ 1
መስከረም – የካቲት 1965

# መግቢያ

የኢትዮጵያ ተማሪዎች እንቅስቃሴ በሚገኝበት ልዩ ሁኔታና ጊዜ ምክንያት 'ከአቅሙ በላይ የሆኑ' አውን ጥያቄዎችን እያነሳ መልሳቸውን ከሞላ ጎደል ሰጥቷል:: ከነዚሁ ጥያቄዎች አንዳንዶቹን ለመጥቀስ ያህል 'መሰረታዊ ለውጥ': 'የብሄሮች ጥያቄ': 'በኢትዮጵያ የሚደረገው አብዮት አይነትና ጠባይ'... ወዘተ. የመሳሰሉት ናቸው::

እነዚህን ሁሉ አርእስቶች ትክክለኛ መልሳቸውንና ገባራዊ መፍትሄያቸውን ማግኘት የነበረባቸው በአብዮታዊ የፖለቲካ ፓርቲ አማካኝነት ነበር:: ነገር ግን ይህን አይነት ድርጅት በኢትዮጵያ የፖለቲካ መድረክ ገና ብቅ ባላለበት የተማሪ እንቅስቃሴያችን ሀላፊነቱን እንዲወስድ ሁኔታው አስገድዶታል::

ለምሳሌ ጊዜያዊ በነበረው በብሄሮች ጥያቄ ላይ ከብዙ ጥናት: ውይይትና ክርክር በኋላ እውነተኛ የሆነ አቋም ለመውሰድ ችሏል:: ይህም ውሳኔ ኢትዮጵያ ውስጥ ለሚካሄዱት ብሄራዊ ትግሎችና ለኢትዮጵያ ብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት የመጀመሪያ ደረጃ እድገት ጥሩ ድጋፍ ሆኖአል::

ጉባኤው ያሳለፈው ውሳኔና ያስከተለው ውጤት አሰይ የሚያሰኝ ነው:: ነገር ግን ጉዳዩ ከመጀመሪያው ግብ ደርሷል በመባል ባለበት መቆም የለበትም:: በነሀሴ 1963 አ.ም በርሊን ከተማ ውስጥ የተሰበሰበው 11ኛው በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር ጠቅላላ ጉባኤ ካሳለፋቸው ውሳኔዎች አንዱ: ስለብሄር ጉዳይ በየቅርንጫፍ ማህበራት ውስጥ ውይይቱ እንዲቀጥልና መጽሄቶቻችንም በዚሁ አርእስት ላይ ት

ምሁርታዊ የሆኑ ትንተናዎችን እንዲያቀርቡ የሚያሳስብ ነበር::

ከዚህ ሌላ በዚሁ እ.ም. በአሜሪካ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር 19ኛ ጉባኤ ስለብሄሮች ጥያቄ በወሰደው ትክክለኛ አቋም ባለመስማማት አንዳንድ አባሎች የነበሩ ጓደኞች ከማህበሩ መውጣታቸው ይታወሳል:: ያውሮፓውና ያሜሪካው ማህበራት ያሳለፉትን ሳይንሳዊ ውሳኔ በመጻረር እስካሁን ድረስ ስህተታቸውን ለማረምና ከማህበሩ ጋር ያላቸውን ቅራኔ በውስጠ-ማህበር ዲሞክራሲ በመጠቀም ለመፍታት ፈቃደኛ ሳይሆኑ ቀርተዋል::

የስህተታቸው ምንጭ አውቀው ሆነ ሳያውቁ ከተነከሩበት ከገዥው መደብ ርእዮተ አለም የፈለቀ ነው:: "መሬት ተቀረበ"፡ "ባህር መውጫ ጠፋ" ይላሉ የባለጉልት ከበርቴ/ፊውደ ቡርዣ/ ስርአት ወኪሎች:: ስለዚህ በአንድነት ስም ህዝቡ ይጨፍጨፍ ይላሉ:: መሬቱ ገንዘቡ እንጂ ሰው አይታያቸውም:: የተቃዋሚያችን ጓደኞች እርስ በእርሱ የሚቃረን አቋም ደግሞ በቀላሉ አቋም ቢገለጥ፡ ስለነጻነት የተናገሩ ነጻነት የሚገኝበትን መንገድ እንደመዘጋት የሚቆጠር ነው:: በሌላ አነጋገር የወደፊቱን ከፍተኛ አንድነት እንደግፋለን ካሉ በኋላ የአሁኑ የጭቁና አንድነት መፍረስ እንደሚያስፈልገው ሲነገር እከኪ ዘራፍ ይላሉ:: እሰሽሹም ዘር እሉ ነው:: በብሄሮች ጥያቄ ላይ የገዥው መደብና የተቃዋሚያች ጓደኞች ልዩነት ያነጋገር ብቻ ሆኖ እናገኘዋለን:: ወደዱም ጠሉም እንዋጋለን የሚሉትን ስርአት መንግስት በተገላቢጦሽ ያገለግሉታል ማለት ነው::



ከላይ የተገለጡትን ምክንያቶች በመመርኮዝ በዚህ የታጠቀ ቁጥር ውስጥ ስለብሄሮች ጉዳይ በሰፊው የሚያብራራ ሀተታ ቀርቦአል:: የጽሁፉ አላማ በመጀመሪያ ትምህርታዊ መልክት ለማስተላለፍ ሲሆን፡ ቀጥሎ ደግሞ የማህበራችንን አቋም የሚቃወሙትን ጓደኞች መሰረታዊ ስህተት በማሳየት አቀጣጫቸውን እንዲለውጡ የሚያስገነዝብ ነው:: ሀተታው ስለብሄሮች ጉዳይ "ተግባብተናል" በማለት ብቻ የሚታለፍ "የመጨረሻ ቃል" መሆን የለበትም:: አንባቢያች አስተያየታችሁን፡ ትችታችሁንና ጥያቄያችሁን በትንተና ወይም በደብዳቤ መልክ ብታቀርቡልን ጥሩ የሀሳብ መለዋወጥ ሊያስከትል ይችላል::

ታጠቅ

# የብሄሮች ጉዳይ በኢትዮጵያ

ዛሬ የኢትዮጵያ ህዝብ በሙሉ ከተተበተበበት የጭቆና ተላቀቀ በሰላምና በነጻነት የሚኖርበት አዲስ ኑሮ ይጠይቃል::በሀብታምና በለምለም አገር ሳሉን አንጠፍጥፍ የሚኖር ህዝብ ከረሀብ:ከድህነት:ከበሽታና ከድንቁርና ጨርሶ የተፋታታ ኑሮ ቢጠይቅ ይገባዋል::መብቱም ነው::

ኢትዮጵያ ሀብታም ነች::ህዝቡ ታታሪ ነው:: ኑሮው የተጎባቀለ ቢሆን:ህዝቡ በሙሉ ታጥቆ የሚባክነው ለጥቂት ቱሀሮች የተትረፈረፈ ኑሮ ለማቅረብ በለሆነ ብቻ ነው:: ጥቂት ሰዎች የሀገሪቱን መሬት በሰሞን:በጉልት:በርስተጉልት... ስም የግል ሀብታቸው አድርገው ይዘውታል::እነዚሁ ጥቂት ሰዎች የሀገሪን ህዝብ በሙሉ በተገዥነት እጁና እግሩን ጠፍረው አሰረውታል::ጉልበቱን ይበዘብዙታል:: ይህም ማለት የኢትዮጵያ የተፈጥሮ ሀብትና በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች ጉልበት በመቶ ለሚቆጠሩ ሰዎች ጥቅም እንዲዉል ተደርጓል ማለት ነው::ባጭሩ የኢትዮጵያ ህዝብ ትከሻ ላይ የጠነባ የፊውዳሊዝም ቀንበር ተጭኗል::

ነገር ግን የኢትዮጵያን ህዝብ እንደቱሀን የሚጠጠው ይህ የጉልተኛ ስርአት ዛሬ ብቻውን አይደለም::ከጥቂት ዘመናት ወዲህ የባእዳን ጭቆና ቀንበር በሀገሪቱ ላይ ጥላውን ዘርግቶ አና የጥለን::እነዚሁ ባእዳን ከበርቴዎች ከሀገሪቱ በዝባዦች ጋር በመሻረክና ከነርሱም ጋር በመደጋገፍ ኢትዮጵያን የጥሬ እቃ ምንጭ:የፋብሪካ እቃ ማራገፊያ:የሀብታቸው ማፍሪያና የጦራቸው ማስፈሪያ አድርገዋታል::ይህም ማለት የኢትዮጵያ ህዝብ የተፈጥሮ ሀብት ለባ

አዳን ጥቅም መዋል ጀምሯል ማለት ነው፡፡ የሀገራችን እንዱስትሪና ፋብሪካ በሀገሪው ነጋዴና ታታሪ ሰው እንዳይካሄድና እንዳይበለጸግ መንግስቱ የሚያግዛቸው ባእዳን አስቸግረውታል ማለት ነው፡፡ባጭሩ በኢትዮጵያ ህዝብ ትከሻ የኢምፔሪያሊዝም/በተለይ የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም/ ቀንበር ተጭኗል ማለት ነው፡፡

በኢትዮጵያ ምንም አይነት ደህንነት ለመጣ የሚችለው ፊውዳሊዝምና ኢምፔሪያሊዝም በህዝብ አመጽ ተደምስሰው በነሱ መቃብር ላይ አዲስ ዲሞክራሲያዊ ስርአት ሲመሰረት ብቻ ነው፡፡

አላማው ይህ ሲሆን ለተፈለገው ህዝባዊ ድል በኢትዮጵያ የሚገኙ የፊውዳሊዝምንና የኢምፔሪያሊዝምን ጭቆና የሚቃወሙ ሀይሎች ሁሉ በአንድነት ተሰልፈው መታገል አለባቸው፡፡ ተራማጆች በሙሉ በኢትዮጵያ ውስጥ ለዚህ አላማ ሊረዱ የሚችሉትን ሃይሎች በጥሞና በማጥናት ትግላቸውን መሰብሰብና ማደራጀት አለባቸው፡፡ይህንንም በምናደርግበት ጊዜ "በኢትዮጵያ የፊውዳሊዝም ጭቆና አለ፤ የኢምፔሪያሊዝም ጭቆና አለ" ብሎ መዘጋት ብቻ አይበቃም፡፡ የዛሬይቱ ኢትዮጵያ በዘመኑ የታወቁት የጭቆና አይነቶች በሙሉ በቀደም መልካቸውም ሆነ በአዲስ ጥበብም እየተራቀቁ የተጠራቀሙበትና የሰፈሩበት፣ የጨለማ አገር ናት፡፡ከነዚህም ጭቆናዎች ውስጥ በፊውዳሊዝምና በኢምፔሪያሊዝም ላይ በመደረብ በአንዳንድ ብሄሮች ላይ የተጫነው ዋናው የብሄሮች ጭቆና ነው፡፡

ዛሬ በኢትዮጵያ በርግጥ የብሄሮች ጭቆና አለ፡፡እንዲያውም ዛሬ በኢትዮጵያ ይህ የብሄሮች ጉዳይ በጣም አጣዳፊና የጋለ ጉዳይ ነው ብለን እናምናለን፡፡ የገዥው መደብ



ይህ ጉዳይ ቢድበሰበስለት ይወዳል፡፡እንዲያውም ቢነሳበት አይወድም፡፡ምክንያቱም በኢትዮጵያ ውስጥ አማራ ያልሆኑት ብሄሮች ላይ የሚደረገው ጭቆና ፈጽሞ መስመርና ልክ የሳተ በመሆኑ ትንሿ አንቧን በተሆን ትልቅ ቃጠሎ ልታስነሳ ስለምትችል ነው፡፡

በዚህ ጊዜ ታዲያ የተራማጆች አቋም ምን መሆን አለበት፡፡በአንድ በኩል ተራማጆች ነን እያሉ በሌላው በኩል ደግሞ እንደገዥው መደብ ይህን ታሪክ የወለደውን የብሄሮች እንቅስቃሴ ማድበስበስ ነው?ወይስ በሃገሪቱ ዛሬ የብሄሮች ጭቆና አለ፤ይህም ትክክለኛ የሆነ የብሄሮች እንቅስቃሴ አስከትሏል በማለት ተገቢ ድጋፍ መስጠት? "ዋናው የመደብ ትግል ነው"፤"የብሄሮች ንቅናቄ የትግሉ አንድነትን ያደፈርሳል"፤"የትግል አንድነትን ያፈርሳል"እያሉ በህዝብ ትግል ማላገጥ ነው ወይስ ይህን ትክክለኛ ትግል ተቀብሎ በተቻለ ለኢትዮጵያ ሰፊ ህዝብ በሙሉ እውነተኛ ነጻነትና እውነተኛ አንድነት እንዲውል ተገቢውን መስመር ማስያዝ፡፡

በዚህ ጉዳይ ከጥቂት ጊዜ ወዲህ በኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ ውስጥ ልዩነት መፈጠሩን ሁሉም ያውቃል፡፡በአውሮፓው 11ኛ ጉባኤና በአሜሪካው 19ነኛው ጉባኤ ላይ የተወሰዱትን ትክክለኛ አቋሞች በመቃወም አንዳንድ ጉዶች ከኛ የተለየ አቋም ወስደዋል፡፡እነዚህ ጉዶች በኢትዮጵያ የሚታዩትን ብሄራዊ ንቅናቄዎች ለማቃለልና አብዮታዊ ይዘታቸውን ለማሳነስ የሚችል የተባባተ ፖለቲካ ሲከተሉ ይታያሉ፡፡ከነዚህ ጉዶች ጋር ስለብሄራዊ ንቅናቄዎች ታሪካዊ አመጣጥ፣ስለአብዮታዊ ይዘታቸው ከመደብ ትግል ጋር ስላላቸው ግንኙነት፣ስለትግል አንድነት ጉዳይና በመጨረሻም ብሄሮች የገዛ

አዱሳቸውን ለመወሰን በሳሳቸው መብት ጉዳይ የተለየ አስተ ባበብ እንከተሳለን::

በነዚህ መስመሮች ቀስ በቀስ የሚጠራ ቁመት ልዩነቶች መጨረሻ ላይ ሁለት ልዩ ልዩ ጉዳዮቻችን ያስይዙናል::እና የመረጥነው ጉዳና ዛሬ ለሚፈለገው ትግል ተግባራችንን አጠ ርቶ የሚያሳይና ለረዥሙ ትግላችን ብርሃን የሚሰጥ:የሰፊው ን ህዝብ አንድነት ከብረት የሚያጠነክርና ወደአብዮታዊ ድ ል የሚመራ አቋም ነው::የተቃዋሚዎች ጓዶች 'ቲዎሪ' ግን የጊዜውን ዋና ተግባር በሚገባ አያሳይም::የጊዜውን ዋና ጠላት በሚገባ አይዋጋም::ስለዚህም በተራማጅነት የቀረበ አቋም ቢሆንም ቃሉ የትምክህተኛው:የጊዜውን ትግል የሚሸሸ ው... ሁሉ መሸሸጊያ ዋሻ እንጂ ምንም አይነት የትግል መሳሪያ ነው ሊባል አይችልም::

ሀ/ የብሄሮች ንቅናቄ የጊዜው የኢትዮጵያና የአለም ሁኔ ታ የፈጠረው ትክክለኛ ንቅናቄ ነው::

ብዙውን ጊዜ በኢትዮጵያ 'ስለብሄራዊ ስሜት' ብዙ ሰዎች 'ኢትዮጵያዊነት' ወይም 'የኢትዮጵያዊነት ብሄራዊ ስሜት' ብለው የሚጠሩት የአማራውን ብሄራዊ ስሜት ብቻ ነ ው::በተለይ ደግሞ ከተሜው ንኡስ ከበርቴ አማራ ኢትዮጵያ ዊነትና አማራነት ፈጽሞ ተደበላልቀውበታል::

እርግጥ ከቀርብ ጊዜ ወዲህ በኢምፔሪያሊስቶች መናቁ ና መገፋት እንገብግቦት በሃገር ፍቅር መንፈስ የተነሳሳ ብሄራዊ ስሜት ብቅ ብቅ ማለት ጀምሯል::አማራው ከኢምፔ ሪያሊስቶች የሚመጣውን መራራና አጥፊ ተንኮል ለመቋቋም:ባ



ህሉን ከፍ ለማድረግና ለማበልጸግ:ማንነቱን ለማሳወቅ:ከወ ረሰው ታሪኩ መልካም መልካሙን እየቀሰመ ወደፊት ለመራመድ መሞከሩ ግሩም ነው::ይህ የሀገር ፍቅር ስሜት ከኢምፔሪያ ሊስቶች ነጻ የሆነች አገር ለመመስረት ታላቅ የትግል ሞተ ር ይሆናል::ይህ ጥቁናን የሚቃወም ትክክለኛ ብሄራዊ ስሜ ት ነው::

ነገር ግን በገዥው መደብ ቁንጮዎች የተነዛ:በኢትዮ ጵያ ያሉትን ሌሎች ብሄሮች የሚንቅና የሚያንቋሽሽ:የአማራ ውን ባህል የበላይነት የሚሰብክ አድሃሪ የሆነ ብሄራዊ ስ ሜት አለ::ይህ አድሃሪና ከሌሎች በላይ ነኝ የሚል ስሜት ስለሆነ ትምክህተኛ/ሸቪኒስት/ ብሄራዊ ስሜት እንለዋለን:: እንዲህ አይነቱ አማራነትንና ኢትዮጵያዊነትን ፈጽሞ የሚያ ደበላልቅ የኢትዮጵያን የሀገር ልብስ 'ልልበስ' ያለ እን ደሁ የሚያጠልቀው የአማራውን ሸማና አጀ ጠባብ ነው:: የኢት ዮጵያን የሀገር ዘፈን 'ልስማ' ያለ እንደሆን 'አምባሰልና ትዝታ' ና ቸው ትዝ የሚሉት:: የኢትዮጵያን የሀገር ምግብ 'ልብላ' ቢል ጤፍ እንጀራ:ደሮ ወጥ:ምንቸት አብሽ ና ቸው ሸው የሚሉበት:: የሀገር ባህል ይጠበቅ ቢል የደገናዉን የ አበሻ ክርስቲያን ባህል ለማስከበር መነሳቱ ነው::በዚህ መልክ አውቀውም ሆነ ሳያውቁ ኢትዮጵያዊነትንና አማራነትን የሚያማቱ ሁሉ በልዩ ልዩ ባህሎች:ቋንቋዎች:ሃይማኖቶች:በ ተዥጎረጎረችው ኢትዮጵያ ለመላ ተበዝባዦች ነጻነት፣አንድነ ትና እድገት ለሚደረገው የጋራ ትግል ፈጽሞ አደገኛ ና ቸው::

ዛሬ በኢትዮጵያ በዚህ የአማራ የበላይነት ብሄራዊ ስሜት በመመራት 'የኢትዮጵያ ህዝብ አንድ ታሪክ ያለው:

አንድ ባህል ያለው፡በአንድ አይነት ብሄራዊ ስሜት የተባበረ ነው' እያሉ በየአቅጣጫው የተሰበጣጠረውን የሀገሪቱን ሁኔታ የሚክዱ ሁሉ የኢትዮጵያን ተበዝባዦች እውነተኛ ነጻነትና አንድነት ጠላቶች ናቸው።

መታወቅ ያለበት አንድ ግልጽ ነገር አለ።በኢትዮጵያ ከአማርኛ ሌላ ቋንቋ የሚናገሩ፡ከሀበሻው ታሪክ ሌላ የራሳቸው ታሪክ ያላቸው፡ከክርስትና ሃይማኖት ሌላ የተለየ ሃይማኖት የተቀበሉ፡ከደገኛው አበሻ ስልጣኔ ሌላ የራሳቸው ስልጣኔ የሚያኮራቸው ሌሎች ብሄሮች አሉ።ከነዚህም በዙዎቹ ከመቶ አመታት ወዲህ ተወርረው በሃይል የተያዙና አሁንም በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ በጦር ሃይል ታስረው የሚገኙ ናቸው።እነዚህ ብሄሮች በተያዙበትም ወቅት ሆነ አሁንም እጅግ ከፍ ያለ ግፍና ውርደት የሚደርስባቸው ናቸው።ግን እነዚህን እውነቶች መቀበል ብቻውን በዙ ዋጋ የለውም።እርግጥ ነው፡እነዚህን እውነቶች መቀበል፡የጊዜው ስርአት የሚነዛቸውን አንዳንድ አስከፊ ፕሮፓጋንዳዎች ወዲያውኑ ፉርሽ ያደርጋቸዋል።ለምሳሌ ከኢትዮጵያ ህዝቦች ግማሹ ያህል በክርስትና አያምንም።ይህ ሲታወቅ ኢትዮጵያን 'የክርስቲያን ደሴት' የሚያደርጋት ቀጥ ያለ ፈሊጥ ክርስቲያን ያልሆኑትን ኢትዮጵያዊያን ጨርሶ እንደሌሉ እየቆጠረ የሚያዋርዳቸው ስድብ ነው።በዚህ መልክ የአበሻውን ክርስቲያን ስልጣኔ ያላዋሃዱ በንጉስ ነገስቱ ግዛት ውስጥ የሚኖሩ ብሄሮች ሌላ መሽት አይነት ጭቆናና ውርደት አለባቸው።

ኢትዮጵያ በየአቅጣጫው የተጐረጐረች አገር ነች ካልን በኋላ በግዛቷ ውስጥ የሚገኙት አብዛኞቹ ህዝቦች ቋ



ንቋቸው የተከለከለ፡ሃይማኖታቸው የተናቀ፡ታሪካቸው የተሰረዘ፡ባጭሩ 'ዝቅተኛ' ህዝቦች በመባል በድንቁርናና በድርብርብ ጭቆና የተያዙ መሆናቸውን ማመን ያስፈልጋል።

ይህን እውነት ካልተቀበልን አንዳንድ ብሄሮች ይህን ድርብርብ ጭቆና ለመቋቋም ከአማራው ብሄር ቀድመው መደራጀታቸውና መነሳታቸው ሊገባን አይችልም።ስለዚህ የንቅናቄው መነሻ እነ ሃይለስላሴ እንደሚሉት የአንዳንድ 'አብሪተኞች' ስራ ወይም 'የውጭ እጅ' ያስነሳው አናደርገውና ቁጭ እንላለን።ከዚያም ደግሞ 'በተራማጆች' ትንተና የሚቀርበለ ረቂቅ ያለ ቴዎሪ አለ።አነጋገሩ ቢለወጥም ግቡ ከላይ ከጠቀስነው ምንም ያህል የማይለይ።

አንዳንድ ጓዶች የብሄሮች ጉዳይ የጊዜው የኢትዮጵያና የአለም ሁኔታ የፈጠረው ትክክለኛ ንቅናቄ ነው የሚለውን አነጋገር ለማፍረስ ይህን ንቅናቄ በጥንቱ በፊውዳሊዝምና/በጉልታዊው ስርአትና/ በከፍለ ሀገር መልኩ/በሪጂናሊዝም/ ብቻ ለወበኑት ይመክራሉ።ይህ አነጋገር በጠቅላላው በዘረደቱ ኢትዮጵያ ብሄራዊ ንቅናቄዎች ያላቸውን መልክና ወደፊት ደግሞ ስለአስተዳደጋቸው ያለንን አስተያየት የተሳሳተ ጎዳና ያስይዛል።

ከሁሉ አስቀድሞ ዛሬ በኢትዮጵያ የሚታዩትን ብሄራዊ ንቅናቄዎች ሙሉ በሙሉ ከጥንቱ የፊውዳሊዝምና የከፍለ ሀገር ግጭት ጋር ማዋሀድ አይቻልም።እርግጥ በጥንቱ ሁኔታ ግጭት ሲደረግ የጎጃም ንጉስ ከሸዋ ንጉስ፡የስሜኑ ከትግሬ፡የላስታው ከሸዋ ነበር።በርግጥ ይህ ከጉልታዊው ስርአት/ፊውዳሊዝም/ ጋር የተቆራኘ፡ከፍለሀገር ከከፍለ ሀገር፡ንጉስ

ከንጉስ፣ባላባት ከባላባት የሚጋጭበት ገትርክ ነበር፡፡በዚህ ላይ ደግሞ ክፍለ ሀገር ከክፍለ ሀገር አያሉ ሸዋን ከጉጃም፣ሰሜንን ከሸዋ፣ሸዋን ከትግሬ በክፍለ ሀገር ቢያጋጩትም 'ከላይ' ያሉት በጋብቻ እየተባበሩ የጠበቀ አንድነት እንደነበራቸውና አሁንም በመጠኑ አንዳንዶቻቸው ግልጽ ነው፡፡ ይህ ሁሉ እውነት ነው፡፡ታዲያስ ምን ይደረግ፡፡እና እንደምናየው ይህ ሁሉ ዛሬ ከተያዘው ትግል አምብዛም ግንኙነት የለውም፡፡

ያሉትን ብሄራዊ ጭቆናዎች በክፍለሀገር ግጭት/በሪጅናሊዝም/ ብቻ ወስነው ለማቅረብ ሲሞክሩ እነዚህ ጓዶች ኢትዮጵያን ከደገናው አበሻ ጋር አደባለቁት፡ የዛሬዩቱን ኢትዮጵያ በደገናው አበሻ ወስነው ቆሞ ይላሉ፡፡ይህንንም በሚያደርጉ በጠቅላላው የዛሬውን የንጉስ ነገስቱን ግዛት ግማሽ አካል/ማለት አንዳል ደጡጡን/፡ የኤርትራንም አንዳንዱ ክፍሎች ከትንተናው ሪስተዋቸው ያልፋሉ፡፡'አንዳንጋጪ' ሆና ደግሞ ብሄራዊ ጭቆናን ለመቋቋም ተደራጅተውና መሳሪያ ነዘው የሚታገሉት ብሄሮች የሚገኙት በነዚህ ክፍሎች መሆኑን እና ያለን፡፡እርግጥ ነው ስለዛሬይቱ ኢትዮጵያ ሁኔታ ትንተና በሚደረግበት ጊዜ እነዚህ ግዛቶች 'ከተረሱ' በኢትዮጵያ ያሉት ጭቆናዎች 'ብሄራዊ' መልክ አላቸው ለማለት ያስቸግራል፡፡ጉጃሜ ከጉንደሬ ቢጣላ የክፍለሀገር ግጭት እንጂ የብሄሮች ግጭት አይደለምና፡፡እና ግን ከዛሬይቱ ኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ በለምንነቱ፣ብሄራዊ ጭቆናዎ ያሉባቸውን ግዛቶች ሁሉ ከትንተናቸን በማስወገዱ፣የክፍለሀገር ግጭት ያለባቸውን ግዛቶች ብቻ ትንተናቸን ውስጥ በማስገባት



'ንኑው' የክፍለ ሀገር ግጭት ነው'እያልን ቸንናቸንን አገዘጋም፡፡

እንዲህ አይነቱ ትንተና ዛሬ በኢትዮጵያ ያሉትን ብሄራዊ ጭቆናዎች የሚያናንቅ፣ትራጭ ይዘታቸውን የሚስት፣የወደፊት ታጋይነታቸውን የማያይ የተሳሳተ ቲዎሪ ነው፡፡

ምክንያቱ፡፡ምክንያቱም ይህን ቲዎሪ የሚያቀርቡት ጓዶች እንደሚያደርጉት ጭቆናዎችን በክፍለ ሀገር ወይም በሪጅናል ጋልጋቸው ከወሰንናቸው ጥንት ባላባቶች ከባላባቶች፣ነገስታት ከነገስታት ከሚያደርጉት ግጭት ለመለየት ፈጽሞ ያዳግተናል፡፡ስለዚህ የነዚህን ጭቆናዎች ጸረፊውዳል ይዘት እንዳናየው ያደርገናል፡፡ግን የዛሬው ልዩ ነው፡፡

በዛሬው ወቅት ጥንት በክፍለ ሀገር ግጭት ዘመን ያልነበረ፣በሌሎች ብሄሮች ላይ የአማራውን ብሄር ባህል ለመጫን የሚጥር መሀከለኛ መንግስት አለ፡፡ጥንት በክፍለ ሀገር ግጭት ዘመን ያልነበረው የካፒታሊዝም ወምጣት፣ያመጣውና ወደፊትም የሚያመጣው መቀራረብ አለ፡፡ይኸውም የካፒታሊዝም ወደኢትዮጵያ መግባትና ስር መስደድ የሚፈጥራቸውና የሚያጋጫቸው ከበርቴዎች/ካፒታሊስቶች ወይንም ቡርዧዚዎች/ በብሄሮች መካከል ያለውን ግጭት እያከረሩት እንደሚሄዱ ጥርጥር የለውም፡፡

በዚህ መስመር ለምሳሌ የጊዜው መንግስት ባለስልጣን ከበርቴዎችና/ቢሮክራቶችና/ ሶቁ ልዩ ተጠቃሚዎች ካፒታሊዝምን ለማስፋፋት የሚያደርጉት መንጠራራት ወደጉጃምና ወደቤጌምድር ሳይሆን ወደአዋሽና ወደአዋሳ /ማለት ወደተጨቆኑት ብሄሮች ግዛት/ እንደሆነ ለመረዳት አያቅትም፡፡ይህን ከተ

ረዱ ደግሞ የነዚህ ብሄሮች ህዝብ ጭቆናን ለመቋቋም የሚያደርገው ትግል ወደፊት በኢትዮጵያ 'የብሄሮችን ጉዳይ' ምን ያህል እንደሚያከረው ለመገንዘብ በእውነቱ ምንም ያህል አዳጋች ጉዳይ አይመስለንም::

በዛሬው ወቅት በኢትዮጵያ ብሄራዊ ጭቆናን ለመቋቋምና ንቅናቄዎችን ለመምራት ጥንት በክፍለ ሀገሩ ግጭት ዘመን ያልነበሩ በባለባቶች ሌላ አዳዲስ ሀይሎች ተፈጥረዋል:: በእነዚህና በሌሎችም መሰል ሁኔታዎች የተነሳ በዛሬይቱ ኢትዮጵያ የሚደረጉት ንቅናቄዎች ከፍለሀገርን እያቋረጡ የተጣራ ብሄራዊ መልክ ቢይዙ እናያቸዋለን::

ዛሬ በኢትዮጵያ ኦሮሞው ከኦሮሞው: አማራው ከአማራው: ሲበለፍ እናያለን:: ወደፊት ደግሞ ይህ በሰፋ እየተጣራ የሚሄደው በብሄራዊ መልኩ እንጂ በክፍለ ሀገር መልኩ እንዳልሆነ ግልጽ ነው:: ከእንግዲህ የባሌው ኦሮሞ ከሸዋው ኦሮሞ አይዋጋም:: ከእንግዲህ የትግሉ መነሻ ቃል 'ኢልሞ ኦሮሞ ቶኮ' ነው:: ይህን ሁኔታ መዘና ተራማጁ ይዘቱን ከአድሃሪ ሃይሉ ለይቶ መተንተና ለትግላችን ያለውን አስተዋጽኦ ሆነ አንቀፋትነት ጠንቅቆ መረዳት ያስፈልጋል::

ይህን እውነት ካልተቀበልን ምንም ነገር ሊገባን አይችልም:: የጉዳዩን መነሳት ከባሌ መነሳት እንደሚነገው አገለየውም:: ሁሉም 'ከፍለሀገሮች' ናቸውና:: የሸዋው ኦሮሞ ከባሌው: ከአሩሲው ኦሮሞ ሲተባበር ግራ ይገባናል:: ልዩ ልዩ 'ከፍለ ሀገሮች' ናቸውና:: ይህን እውነት ካልተቀበልን በተጨቆኑ ብሄሮች ላይ ያለውን ድርብ ድርብርብ ጭቆና: ይህም ደግሞ ለትግሉ የሚሰጠውን የመነሻ ሃይል ፈጽሞ ልናየው



ስንችለም:: ብሄራዊ ንቅናቄን እንንያቸዋለን::

ስንት ናቸው ዛሬ ከዚህ የተሳሳተ እምነት ተነስተው ይህንን በመሰረታዊ ጉዳዮች ተነሳስቶ የሚታገለውን ህዝባዊ ንቅናቄ 'ከነሃይለስለሴ ጋር በጥቅም የተጋጩ ባላባቶችና ከበርቴዎች' ብቻ ተገፋፍቶ የተነሳና እነዚሁ ጥቅም ፈላጊዎች እንዳሰኛቸው በገ አለም የሚያደርጉት ንቅናቄ የሚመስላቸው:: ስንቶቹስ ናቸው የጠቅላላውን ንቅናቄ መሰረታዊ ጸረፊውዳልና ጸረኢምፔሪያሊስት ይዘት የሚስቱ:: የጠቅላላውን ንቅናቄ ዘላቂነት የሚያቃልሉ::

ለኛ ጥያቄው በጣም ግልጽ ነው:: በመጭው ጊዜ አድሃሪዎች የተበዘበዙትን ትግል ለመቋቋም በሰፊው ህዝብ መሀከል የፈጠሩትን ጥላቻና አለመግባባት በማባባስና ተጋግዞን ህዝብ እርስ በርሱ በማጋጨት የነጻነቱን ትግል ለመከፋፈልና ለማዳከም አይመለሱም:: በተራማጆች በኩል ይህን ቅራኔ ማናናቅ የሰጎን ፍልስፍና ይሆናል:: አድሃሪዎች በዚህ ቅራኔ በመጠቀም ፍጅትና ትርምስ ፈጥረው የጋራ የሆነውን የነጻነት ትግል እንዳያስናክሉት ተራማጆች በሙሉ ተጋግዘው ሰፊው ህዝብ ከተዘረጋለት ወጥመድ ውስጥ እንዳይገባ መታገል ታሪክ የጣለባቸው ከባድ ሃላፊነት ነው::

አለበለዚያ የኢትዮጵያ ሰፊ ህዝብ አድሃሪዎች ከሚዘረጉለት ትርምስ ውስጥ እጅና እግሩን ታስሮ: ህሊናው ተመርዞ ከገባ በኋላ ማንኛውም ተበዝባዥ በጠባብ ብሄሩ ተውተብትቦ የመላ ኢትዮጵያን ተበዝባዦች መሰረታዊ አንድነት: ዋናውን የበዝባዥና የተበዝባዥ ትንንቅ: እውነተኛውን የነጻነት ትግል ረግጦ ሊያልፍ ይችላል:: በዚህም ትርፍ ትርምስ

ይበልጡን የሚነዛው መጠላላት፡ይበልጡን ስር የሚሰደው ቂምና በቀል፡ይበልጡን የሚመጣው ደም መቃባት መጨረሻው ለማይታይ ረዥም ጊዜ የኢትዮጵያን ተበዝባዦች ባለመግባባትና በደም ገንቦ ሊከፋፍላቸው ይችላል።።ይህ ሁሉ ሲሆን በመሰረቱ ጸረፊውዳልና ጸረኢምፔሪያሊስት የሆነው የተበዝባዦች ትግል ሊዘበራረቅና ለጊዜው ሊከሽፍ ይችላል።።ይህ ሁሉ እንዳይሆን ጊዜው የሚጠይቀውን ፖለቲካ በመረዳት ተራማጆች ሁሉ ሀላፊነትን መቀበል አለባቸው።።ዛሬ በኢትዮጵያ ተበዝባዦች መካከል ያለውን ቅራኔ ልኩን በመገንዘብ ትግሉን ለማራመድ የማይቀጠብ ጥረት ማድረግ ተገቢ ነው።።ለዚህም ከሁሉ አስቀድሞ የብሄሮች ጭቆና የወለደውን ንቅናቄ በዛሬው ወቅት ታላቅ አብዮታዊ ይዘት እንዳለው መረዳት ያስፈልጋል።።በዚህ አብዮታዊ ይዘትም ለመላ ኢትዮጵያ ተበዝባዦች ነጻነት መጠቀምን ማወቅ አለብን።።

ለ/ የብሄሮች ንቅናቄ በዛሬይቱ ኢትዮጵያ ታላቅ አብዮታዊ ይዘት አለው

ዛሬ በኢትዮጵያ የሚታዩት የብሄሮች ንቅናቄዎች ማንም ይምራቸው ማንም ከስርአቱ የተቀረኘውን የፖለቲካ ጭቆናን ስለሚዋጉ፡ለሙሉ እኩልነት ስለሚታገሉ፡በተለይ በደቡብ ግዛቶች ከመሬት ጉዳይ ጋር በጥብቅ የተያያዙ በመሆናቸው መጀመሪያ ላይ ለማንቀሳቀስና ለማደራጀት አስቸጋሪ የሆነውን ገበሬ ለማነሳሳት ስለሚረዱ፡ሰራተኛውን፡ንኡስ ከበርቴውንና አገረ ወዳድ ከበርቴውን፡እንዲሁም አገር ወዳድ ባላባቶችን አጠቃለው የሚይዙ ሰፊ ንቅናቄ በመሆናቸው አብዮታዊ ይዘት አላቸው።።



ይህ ትግል የተጨቆኑ ብሄሮች በወረራ የተቀሙትን መሬታቸውን ለማስመለስ ብቻ የተነሱበት ሳይሆን፡በብዙ ዘመናት ውርደትና ጭቆና በራሳቸው ያጡትን እምነትና ኩራት መልሰው ለመጎናጸፍ የታጠቁበት ትግል ነው።።በኢትዮጵያ በአርግጥ እስላሙ ከክርስቲያኑ፡ኦሮሞው ከአማራው ... እኩል የሚሆነው በዚህ ለሙሉ እኩልነት ታጥቆ በተነሳ ትግል የጊዜው ስርአት ተደምስሶ ሲወድቅ ብቻ ነው።።ንቅናቄው ታላቅ አብዮታዊ ይዘት አለው የምንለው ከግቡ ለመድረስ ሲታገል ስርአቱን ያፈራርሰዋል የሚል የጠበቀ እምነት ስላለን ነው።።

የአንድ ንቅናቄ አብዮታዊ ይዘት የሚለካው ወቅቱ፡አካባቢውና ተጨባጩ ሁኔታ እየተመዘነ ነው እንጂ እንዲሁ ዝም ብሎ በባዶ ቦታ አይደለም።።በደፈናው አብዮታዊ የሚባል ነገር የለም።።ስለዚህ የብሄሮች ንቅናቄን አብዮታዊ ይዘት ስንመዝን ከዛሬይቱ ኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ መነሳት አለብን።።

በዛሬይቱ ኢትዮጵያ መላው ህዝብ ለዘመናት በተጫነው የጨለማ አገዛዝ የታፈነ ስለሆነ የፖለቲካ ንቃቱ ከመጠን በላይ በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል።።የተደራጀ የፖለቲካ ተቃውሞ ለምዶ የለውም።።በዚህ ላይ ደግሞ ዛሬ የጊዜው ስርአት ከኢምፔሪያሊስቶች ገጥሞና በነሱም እየተገዛ ፈጽሞ የማይደፈር መስሎ ይታያል።።በሃገሪቱ የሚነሳውን ማንኛውንም የፖለቲካ ንቅናቄ ለመመዘን ከዚህ እውነት መነሳት ያስፈልጋል።።ይህን ዝቅተኛ የትግልና የንቃት ደረጃ ተወጥቶ በማንኛውም መልኩ ቢሆን ጭቆናን ለመቋቋም የሚሰነዘረው ማንኛውም የተደራጀ ትግል የስርአቱን መሰረት ለማናጋት ከሚ

ያበረለገው ናዳ እንደ አንዱ ደሀና ዱንጋይ ሊቆጠር ይገባዋል::በተለይ ብሄራዊ ንቅናቄዎች ለብዙ ዘመናት ተደላድለው የተቀመጡትን አስባሪ እምነቶችና/ማለት ዘውዱን: የቤተክህነትን የበላይነት: የመሬቱን ስሪት: የአማራውን የበላይነት: .../ ለመቋቋም የሚነሱ እንቅስቃሴዎች በመሆናቸው ማንም ሊንቀው የማይችለውና የማይገባው አብዮታዊ ይዘት አላቸው::

አንዳንድ ሰዎች የነዚህን ንቅናቄዎች አብዮታዊ ይዘት ለማቃለል 'በሃይማኖት ላይ የተመሰረቱ ናቸው': 'በነገድ ስሜት ላይ የተመሰረቱ ናቸው' ይላሉ::ግን እንደዚህ አይነቱ ማወናበጃ ፈጽሞ አያሸብረንም::ዛሬ በኢትዮጵያ 'እስላሙ በሃይማኖት ላይ ተመስርቶ' ቢነሳ አስቀድሞ ስርአቱ በሃይማኖት ልዩነት ላይ የተመሰረተ ጭቆና ስለሚያደርግ ነው::የሃይማኖትን እኩልነት መጠየቅና ለሱም መታገል ደግሞ የጊዜውን ስርአት አንጠልጥለው ከያዙት የአይዲዮሎጂ/የርእዮተአለም/ ምሰሶዎች/ማለት የቤተክህነት የበላይነት/ ማናጋት ነው:: ሃይለኛ አብዮታዊ ይዘት አለው:: የምንደግፈውም ይህንን አድልዎ ደምስሶ እኩልነትን ለመፍጠር ሲታገል ነው::በዚህ መልክ እነዚህ ንቅናቄዎች 'በነገድ ልዩነት' ላይ ተመሰረቱ ቢባልም መልሳችን ያው ነው:: ትግላቸው በአማራው ገዥ መደብ የተቋቋመውን አንዱን 'ነገድ':በአንዱ ላይ የሚያደርገውን "የነገድ ልዩነት" ለመቋቋም ነው:: የምንደግፈውም 'የነገድ' ጭቆናንና አድልዎን ደምስሶ ሙሉ እኩልነትን ለመመስረት ሲታገል ነው::

አንዳንድ ጓዶች ደግሞ 'የብሄሮችን' ንቅናቄ አብዮታዊ ይዘት ለማቃለል 'ጸረፊውዳልና ጸረኢምፔሪያሊስት' ፕሮግራም



የላቸውም::መሪዎቹ ከበርቴዎችና ንኡስ ከበርቴዎች ናቸው:: አንዳንድ ጊዜ እንዲያውም ባላባቶች ይመሩታል::ስለዚህ በእነዚህ ታሪክ ባለፋቸው ሃይሎች የሚመራ ንቅናቄ አንደግፍም" ይላሉ::እንደሚመስለን ብዙ ጓዶች የተደበላለቀባቸው እዚሁ ላይ ነው::

ነገር ግን እስከ 'የብሄሮች ንቅናቄ' ሲባል ምንም ጊዜ ቢሆን እነሱ ላይ የሚመራው በከበርቴዎች:በንኡስ ከበርቴዎችና እንዲያውም በአንዳንድ አገር ወዳድ ባላባቶች ነው::እርግጥ ነው በዛሬው ወቅት በየትም ያለ ከበርቴ መደብ ህዝቡን አነሳስቶ እስከመጨረሻው ድረስ ወደዲሞክራሲ መምራት አይሆንለትም::ትግሉን እስከመጨረሻ መምራት ይቅርና በወጉ መደገፍ እንኳን አይሳካለትም::እርግጥ ነው በዛሬው ወቅት ማንኛውም ንቅናቄ አብዮታዊ ግቡ የሚደርሰው:ከገበሬው ጋር የሚተጋገዘው ሰራተኛው መደብ ሲመራው ብቻ ነው::በዛሬው ወቅት ዘላቂ አብዮታዊ ሃይል ያለው:ለዲሞክራሲ የሚደረገውን ትግል እንኳን ሳያወላውል እስከመጨረሻ ሊመራ የሚችለው ሰራተኛው መደብ ብቻ ነው::ስለዚህ ማንኛውም ንቅናቄ የተራማጆችን ሙሉ ድጋፍ የሚያገኘው በተጣራ ጸረፊውዳልና ጸረኢምፔሪያሊስት ፕሮግራም ስር ተሰልፎ በሰራተኛው መደብ እየተመራ ሲታገል ነው::

ነገር ግን በዛሬው ጭልምልም ባለ ሁኔታ አንዱን የተጨቆነ ብሄር አሰልፎ የሚታገል ንቅናቄ ከመጀመሪያው ቀልጭ ያለ ፕሮግራም አላወጣህም ብሎ አይንህን ላፈር አይባልም::ስለአስመራሩ ጉዳይ እላይ የሰነዘርነው ሀሳብ ጠቅላላ አቅጣጫ ያሳየናል እንጂ ሁሉንም እውነት/በየጊዜው ሊሆን

የሚችለውን ሁሉ/ አይወስንም፡፡ከበርቴው ትግሉን እስከመጨረሻ አያዘልቀውም ተባለ እንጂ አይጀምረውም አልተባለም፡፡ ሰራተኛው መደብ ትግሉን ከመጨረሻው ግቡ ያዘልቀዋል ተባለ እንጂ ከመጀመሪያው አንስቶ ይመረዋል ወይም መምራት አለበት አልተባለም፡፡

በዛሬይቱ ኢትዮጵያ የጭቆናው መልኩና ልኩ የተለያየ ነው፡፡ስለዚህ ጭቆናን ለመቋቋም የሚነሱት ሃይሎች እጅግ የተሰበጣጠሩ ናቸው፡፡በመጀመሪያ ላይ በነዚህ ልዩ ልዩ ንቅናቄዎች ውስጥ የሰራተኛው መደብ የተደራጀ ሃይል እጅግ የመነመነ ነው፡፡ነገር ግን በነዚህ ልዩ ልዩ ሃይሎች፡በልዩ ልዩ ሁኔታዎች ተገፋፍቶ የተነሳው ትግል ከመሀል እንዳይከሸፍ መጠንቀቅ ያስፈልጋል፡፡ትግሉ የመሪዎቹ ከበርቴዎች፡ንኡስ ከበርቴዎችና አንዳንዴም ባላባቶች ጥቅም ሲረካ ትጥቁ እንዳይፈታ ሌላ አብዮታዊ መሪ ያስፈልጋል፡፡በዚህ ጊዜ ሰራተኛው መደብ በተደራጀ ሃይሉ የትግሉን አርማ ከሚያፈገፍገው ባላባት፡ከሚርበተበተው ከበርቴ፡ከሚወላውለው ንኡስ ከበርቴ እጅ መንጥቆ መውሰድና ከገበሬው በመተጋገዝ አብዮቱን ከግቡ ማድረስ ታሪካዊ አደራው ነው፡

የብሄሮች ንቅናቄ ከዚሁ የተለየ የሚከተለው መንገድ የለም፡፡በያለበት የሚታየው ንቅናቄ አመራር ለጊዜው ከተበዝባዦች እጅ አልገባም፡፡ነገር ግን አሁን ባለበት ደረጃና አመራር ያለውን አብዮታዊ ይዘት ፈጽሞ መሳት አይገባንም፡፡ የሀገሪቱን ተጨባጭ ሁኔታ ፈጽሞ ሳንመለከት፡በያለበት የሚደረገው ትግል የደረሰበትን ደረጃ ፈጽሞ ሳንገነዘብ፡በደፈናው 'ከበርቴው ዘመኑ አልፎበታል' በሚል ፈሊጥ ብንወስን



ለያዝነው ትግል ትልቅ ጉዳት እናመጣለን፡፡ከዳር ቆመን ከማሽሟጠጥ በስተቀር ዛሬ ከትግሉ የምንደባለቅበትን ምንም አይነት ዘዴ ስለማያሳየን እንደዚሁ አይነቱ ቴዎሪ ካለትግል የማይመጣውን ድል ቁጭ ብለን እንድንጠብቅ ያደርገናል፡

በበኩላችን ለኢትዮጵያ ሰፊ ህዝብ ሙሉ ነጻነት ለሚደረገው ትግል ብሄራዊ ንቅናቄዎች በውስጣቸው ያዘሉት አብዮታዊ ይዘት እስኪያልቅ ድረስ ረዳቶች ናቸው የሚል የጠበቀ እምነት አለን፡፡ነገር ግን ትግሉን የቀሰቀሱት ልዩ ልዩ ሀይሎች በሙሉ እስከመጨረሻ እንደማይዘልቁ እናውቃለን፡፡ ስለዚህ አብዮታዊ ይዘታቸው ሲያከትም አመራሩን ሰራተኛው መደብ በተደራጀ ሃይሉ ተቀብሎ መቋረጥ የማይገባውን አብዮት ወደፊት እንዲያራምደው እንታገላለን፡፡

የተራማጆች ዋና ተግባር ይህንን ትግል ሰብስቦ ቀስ በቀስ ጸረፊውዳልና ጸረኢምፔሪያሊስት ይዘትን እያጠራ፡ከሰራተኛውና ከገበሬው አመራር ስር ማስገባትና አብዮቱን ከግቡ ማድረስ ነው፡፡

ብሄራዊ ንቅናቄዎች በውስጣቸው፡እንዲያውም በአመራራቸው ውስጥ ጸረፊውዳልና ጸረኢምፔሪያሊስት የሆነው ፕሮግራም እስከመጨረሻው እንዳይዳብር የሚሞክሩ ሃይሎች እንዳዘሉ አይካድም፡፡ስለዚህ ተራማጆች እነዚህን እንቅፋቶች ለማስወገድ ሳይታክቱ መታገል አለባቸው፡፡ነገር ግን እነዚህ ሃይሎች ዛሬ ትግሉ ባለበት ደረጃና በጠቅላላው በሀገሪቱ ሁኔታ ሲታዩ ለምንታገልለት 'ጸረፊውዳልና ጸረኢምፔሪያሊስት ፕሮግራም' እንደዋናው እንቅፋት ሆነው ሊታዩ/ሊቆጠሩ/ ይገባልወይ፡፡አይገባም፡፡

ይህንን እውነት የሚቃወሙ ኃይሎች ጉዳዩ እንደ
ዚህ ሆኖ አይታያቸውም::በለ'ጸረፊውዳልና ጸረኢምፔሪያሊስ
ት ፕሮግራም መዳበር' በሚያነሱበት ጊዜ ውሳኔው የሚለው
እና ቱም አቢቱም የሚከተለውን ብቻ ነው::'በንኡስ ከበርቴ
ናሽናሊስቶች መደንፋት ሳይወናበዱ . . . የኢትዮጵያ ተራማጅ
በሙሉ ጸረፊውዳልና ጸረኢምፔሪያሊስት የሆነ ፕሮግራም ማዳ
በር አለባቸው::ይህም ማለት ዛሬ በኢትዮጵያ የተያዘው ት
ግል በደንበኛ ተራማጅ መስኩ እንዳይበለጸግ የሚያግዱት ፀ
ና ጠላቶች በብሄራዊ ስሜት ተገፋፍተው:በብሄራዊ ጭቆና ተ
መርረው የተነሱት ብሄራዊ ንቅናቄዎች ሆነው ቀሮ አሉ ማለ
ት ነው::ተቃዋሚያች ኃይሎች እዚህ ላይ 'የምንቃወመው መሪ
ዎቹን ነው' እያሉ 'የማይጠቅሙ' መከራከሪያቸውን ይሰነዝሩ
ይሆናል::ግን እስቲ ስራተኛው መደብ ቀስቀስ:ስራተኛው መ
ደብ ከመጀመሪያው አንስቶ እየመራ ከገቡ ያደረሰው:'ናሽና
ሊስቶች' አስቀደመው ሳይመረት ያደገ ብሄራዊ ትግል አንድ
ይጥራልን::

እናም በንሆን መቸም 'ንኡስ ከበርቴያች ናሽናሊስቶ
ችን' እለል እያልን አንቀበላቸውም::ለተራማጅ አለማችንም
የሚስነዝሩትን አደጋ ፈጽሞ አንስተውም::ስለዚህ እን ታገ
ላቸዋለን::ነገር ግን በዛሬው ወቅት እነሱን እንደዋና ጠ
ላት በመቁጠር ከነሱ ጋር ባለ ሃይላችን እንተናነቃም::ም
ክንያቱም ሌላ ምንም ነገር ሳይሆን እኛና እነሱ የምንተጋ
ገዝባቸው ይበልጥ ሀይለኛ የጋራ ጠላቶች:ይበልጥ አጣዳፊ
የጋራ ተግባሮች ስላሉብን ነው::ስለዚህ በዚህ በኩል
እና እንደዋና ጠላት አድርገን የምንወስደውና ባለን ሃይል



ዛሬ የምንተናነቀው የተጨቋኙ ብሄሮች ብቻ ሳይሆን የመላ
ኢትዮጵያ ህዝብ ጠላት የሆነው:አድሃሪያቹ የሚነዙት ትምክ
ህተኛ ብሄራዊ ስሜትን ነው::

## የብሄሮች ትግልና የመደቦች ትግል

ከብሄሮች ትግል ተቀዳሚነት የሚስጠውና ይበልጥ መሰ
ረታዊ የሆነው የመደቦች ትግል ነው::በኢትዮጵያ ዋናው ት
ግል በንጉስ ነገስቱ ግዛት ውስጥ የሚገኙት ተበዝባዦች በ
አንድ በኩል:በዝባዦች ደግሞ በሌላው በኩል ሆነው የሚሰለ
ፋበት የነጻነት ትግል ነው::ይህ ማለት ለምሳሌ የኤርትራ
ተበዝባዥ ህዝብና የአማራ ተበዝባዥ ምንም አይነት መሰረታ
ዊ የጥቅም ግጭትና ጠብ የላቸውም::የኤርትራ በዝባዦችና
የአማራ በዝባዦችም 'ሌባ ከሌባ ቢጣላ በሰው ገለባ' እን
ደሚባለው በዘረፋው ድርሻ ቢጣሉም ምንም ያህል መሰረታዊ
ግጭት የላቸውም::

የኢትዮጵያ ተበዝባዦች በሙሉ ፊውዳሊዝምንና ኢምፔሪ
ያሊዝምን የሚያህሉ የጋራ ጠላቶች አሉባቸው::የኢትዮጵያ
በዝባዦች በሙሉ አብዮትን ያህል:ህዝቡን ያህል የጋራ ጠላ
ት አለባቸው::መሰረታዊው እውነት ይህ ነው::

ይህንን ስንል በሰፊው ተበዝባዥ ህዝብ መሀከል አ
ለመግባባትና የጊዜ ግጭት የለም ማለታችን አይደለም::ይህ
አለ::ነገር ግን ተበዝባዦች ምን ጊዜም ቢሆን የጋራ ጥቅ
ማቸው ከልዩነታቸው ያመዝናል::ከበዝባዦች ጋር ባላቸው ጠ
ብ አኳያ ሲታዩ በእውነት በመሀከላቸው ያለው ግጭት በቀላ

ሉ የሚገመት፡በእርቀና በስምምነት ሊያልቅ የሚችል ጉዳይ ነው፡፡ሰፊው ህዝብና በዝባዦቹ ግን አባትና ጭድ ና ቸው፡፡ ፈጽሞ ሊታረቁ አይችሉም፡፡ስለዚህ ይህ ግጭት በቀላሉ የሚገመት አይደለም፡፡በአንደኛ ደረጃ መታየት ያለበት ዋና ቅራኔ ነው የምንለው ለዚህ ነው፡፡

ይህ ሳይገባን የተመረከዘ መሰረታዊ እውነት ነው፡፡ ነገር ግን በዝባዦች የነሱን አንድነት ለመሸሸግ፡የሰፊውን ህዝብ አንድነት ለማፍረስ የማይሞክሩት የላቸውም፡፡በዘረፋው ጉዳይ እርስ በእርስ በተጋጩ ቁጥር መሳሪያም ያደርጉታል፡፡በጠቀላላው ለነሱ የሚያመቻቸው ጥላቻ፡መናናቅ፡አለመግባባት፡አለመተማመንና ደም መቃባት ስር ቢሰድና ሰፊው ህዝብ ቢከፋፈልላቸው ነው፡፡አንዳንድ ጊዜ በዚህ በከፋፍለህ ግዛ ፖለቲካቸው የተነሳ ሰፊው ህዝብ ከመጠን በላይ ይከፋፈልና እውነትም መሰረታዊ አንድነቱ ለብዙ ዘመናት ሊደበስበስና እንዳልነበረ ሆኖ ሊጠፋ ይችላል፡፡በእንደዚህ አይነቱ ወቅት እንደናይጀሪያ፡አሁን በቅርቡ ደግሞ እንደሩዋንዳ ተበዝባዥ በተበዝባዥ ላይ እየተነሳ ሲተራመስና ሲተላለቅ የመደብ አንድነትና የመደብ ትግል ይረሳል፡፡በዚህም ሰክ ደግሞ የመላ ተበዝባዦች የእውነተኛ ነጻነት ቀን እየራቀ ይሄዳል፡፡ዛሬ በኢትዮጵያ ካሉት ተራማጆች ተገቢ እርምጃ ቸን ካልወሰዱ ወደዚህ ትርምስ የምንመራበት አደገኛ ሁኔታ አለ፡፡ ተራማጆች ሁሉ ይህንን እውነት በመረዳት ይህ ከንቱ ትርምስ ታግዶ ትግሉ ወደእውነተኛ የነጻነት ትግል እንዲለወጥ መጣጣር አለባቸው፡፡

አቋማችንን የሚቃወሙ ጓዶች 'በደፈናው' ትክክል የ



ሆነውን 'ዋናው የመደቦች ትግል ነው፡፡በብሄሮች መሀከል ያለው ቅራኔ የሁለተኛ ደረጃ ቅራኔ ነው፡፡ የብሄሮች ትግል ለመደቦች ትግል መታዘዝ አለበት፡፡ለሱም ቅድሚያ መስጠት አለበት፡፡' የሚለውን አነጋገር በየውሳኔያቸውና በየጽሁፋቸው ያወርዱታል፡፡ሳይገባን የተመረከዘ የህብረተሰቦች እርምጃ ህግ አበጥሮ እንደሚያስረዳን የመደቦች ትግል መሰረታዊ ቢሆንም በአንድ በተወሰነ ታሪካዊ ወቅትና በአንድ በተወሰነ ተጨባጭ ሁኔታ አንጻር ሲታይ መሰረታዊ ያልሆነው የብሄሮች ግጭት የዋናውን ቅራኔ ቦታ ለጊዜው እንደሚይዝ የታወቀ ነው፡፡

<u>በእንደዚህ አይነቱ ጊዜ የተራማጆች ተግባር 'ዋናው የመደቦች ትግል ነው' እያሉ አዋጅ ማስነገር አይደለም፡፡ በዚህ ጊዜ የተራማጆች ተግባር አስቀድሞ ይህ ከመጠን በላይ ተጋግሞ የህዝቡን መንፈስ አውተብትቦ የያዘውን ምንም አይነት የመደቦች ትግልም ሆነ የትግል ትብብር የሚከለክለውን አለመግባባት ለማስወገድ መታገል ነው፡፡በበኩላችን የዛሬው ዋና ተግባር ይህ ነው እንላለን፡፡</u>

ዛሬ በኢትዮጵያ ባሉት በብሄሮች መሀከል ለብዙ አመታት የተጠራቀመ፡በአድሃሪዎቹ የተነዛ የጥላቻና ያለመግባባት ያለመተማመን መንፈስ አለ፡፡በአማራው ገዥ መደብ አጥፊ ፕሮፓጋንዳ በመመረዝ የአማራው ህዝብ የኦሮሞውን፡የጉራጌውን፡የትግሬውን፡የሸንቀላውን፡የኤርትራውን ህዝብ ሁሉ ከመጠን በላይ ይንቃል፡፡በዚህ አኳያ ደግሞ እነዚህ ህዝቦች በአማራው ህዝብ ላይ ትልቅ የጥላቻና የጥርጣሬ ስሜት አላቸው፡፡ ይህ ሁሉ ተደጋግሞ በኢትዮጵያ በብሄሮች መሀከል ታላላቅ አ

ለመግባባት አለ፡፡ይህ አለመግባባት በኢትዮጵያ ጊዜያዊ ሁ ኔታ ከተራ ግጭት አልፎ የዋና ቅራኔ ቦታ በመያዝ ላይ ነ ው የምንለው የመደቦች ትግል ተገቢ ቦታውን እንዳይዝ ስለ ፈነውና የኢትዮጵያ ተበዝባዦች አንድነታቸውን አጠንክረው የጋራ ትግላቸውን እንዳያካሂዱ ስለከለከላቸው ነው፡፡

በዚህ መልክ ዛሬ በኢትዮጵያ የታፈነውንና የተድበሰበሰውን የተበዝባዦች አንድነት ተገቢ ቦታውን ሊይዝ የሚችለው ወቅትንና አካባቢን ጨርሶ በሳተ ፈሊጥ እንደአንዳንደ ቾ ጓደች 'የመደብን ትግል' ቅድሚያ ደጋግመን ብናስማ አ ይደለም፡፡በብሄሮች መሀከል ላለው ግጭት ተገቢ ቦታውን ሰጥተን በቅድሚያ እሱን ለመቀነስ ባለን ሃይል ስንታገል ነው፡፡

ይህን አቋም የሚቃወሙ ጓደች ባባለፈት ውብኔ ላይ የመደብ ትግል ቅድሚያ መስጠት እንዳለበት ሲያስረዱ እንዲህ ይላሉ፡፡ 'በንኡስ ከበርቴ ናሽናሊስትስ ዱንፋታ... ቢይወናቢዱ የኢትዮጵያ ተራማጆች በሙሉ ... የብሄሮች ጉዳይ ለመደቦች ት ግል ቅድሚያ እንዲሰጥ መታገል አለባቸው፡፡'ይህ እኛም የ ምንስማማበት መሰረተ ሀሳብ/ፕሪንሲፕል/ ነው፡፡ ነገር ግን ይህ አቋም አንደኛ ነገር ዋናውን ጠላት በሚገባ አይለይም፡፡ እንዲያውም ትምክህተኛ ብሄራዊ ስሜትን የሚያግዝ ነው፡፡ሁ ለተኛ ነገር ደግሞ የጊዜውን ተግባር አበጥሮ አያሳይም፡፡ ስለዚህ ለተያዘው ትግላችን ምንም መባሪያነት የሌለው ትግ ልን የሚሸሽ አቋም ነው፡፡

ይህ አነጋገር ዋናውን ጠላት ስቶ፡አድሃሪውን ትምክ ህተኛ ብሄራዊ ስሜት ትቶ ጭቁኑን የሚቃወመውን ብሄራዊ ስ-



ሜት ለማጥቃት ይሞክራል፡፡እርግጥ ነው፡እዚህ ላይ ትግሉ የተጧራ የመደቦች ትግል መልኩን እንዳይዝ 'ለገዢ ብሄረ ብቻ' እያለ አንድነትን የሚሸሸው ጠባብ ብሄራዊ ስሜት አ ንቅፋትነት አለው፡፡ግን አሁንም እንቅፋቱ እሱ ብቻ ነውወይ፡፡ እንዲያውስ በአሁኑ ወቅት ዋናው እንቅፋት እሱ ነውወይ፡፡ በፍጹም አይደለም፡፡ከሱ እኩል፡እንዲያውም ከሱ ይበልጥ ለ መደቦች ትግል ዋናው የጊዜ እንቅፋት የሆነው ገዢው መደብ በአማራው ህዝብ መንፈስ የሚነዛው ትምክህተኛው ብሄራዊ ስ ሜት ነው፡፡ የአማራው ህዝብ የተጨቆኑት ብሄሮች ትግል የሱ ትግል መሆኑ ገብቶት፡የነሱ ድል የሱ ድል መሆኑን ተገንዝ ቦት ከወንድሞቹ እንዲ ደባለቅ፡ቀስ በቀስ እየተጉተተ ከሚ ገባበት ከዚህ ወጥመዱ እንዲፍታታ ያስፈልጋል፡፡በኢትዮጵያ ተበዝባዦቹ በአንድ በኩል፡በዝባዦቹ በሌላ በኩል ሆነው የነጻነቱ ትግል መስመር እንዲይዝ ከተፈለገ አስቀድ ሞ ትምክህተኛ ብሄራዊ ስሜት በኢትዮጵያ ተራማጆች የተባ በረ ትግል መዳከም አለበት፡፡

የብሄሮች ትግል በኢትዮጵያ አሁን ከተድበሰበሰበት ሽርኩቻ ወጥቶ ደንበኛ ቦታውን የሚይዘው የብሄሮችን እኩል ነት ረግጦ የያዘው የኢትዮጵያ ተበዝባዦች በሙሉ ዋና የጊ ዜው ጠላት የሆነው ትምክህተኛው ብሄራዊ ስሜት ሲገታ መሆ ኑ ግልጽ ነው፡፡ይህ እውነት እንደጸሀይ በሬህ ሆኖ እየታ የ ይህን ትቶ ያናውን እጥብቆ ተዋጋ የሚለው አቋም እሀ ያውን ፈርቶ ዳውላውን የሚመታ አቋም ነው፡፡ለትግላችንም አይረባንም፡፡እንዲያውም ያደናቅፈናል፡፡

እፍ አውጥቶ አማራው ህዝብ እስኪነሳ 'አንጠብቅ':

ተነሱ በለን ፊሽካ እስክንነፋ ድረስ 'ባለህ እርጋ' ማለት ቢሳነው የተጨቆኑ ብሄሮች ለትግል ቀድመው መነሳታቸውን እንደዋና እንቅፋት አርጉ መቁጠር ትምክህተኛ ብሄራዊ ስሜት ካልሆነ ምን ቃል ይገኝለታል::

በበኩላችን የመደቦች ትግል በተቻለ ፍጥነት በኢትዮጵያ ተቀዳሚ ቦታውን እንዲይዝ የማይቆጠብ ጥረታችንን አናቋርጥም::ለዚህም የጊዜውን ተግባራችንን ጠቅላላ አዘማሚያ በሚገባ እናውቃለን::ይኸውም ለጊዜው ዋና የምንለው የመደቦች ትግል እንቅፋት መዋጋት ነው::አማራው ህዝብ የተጨቆኑ ብሄሮች ለእኩልነት የሚያደርጉትን ትግል፣ በማደናቀፍ ለጠላቶቹ ለአድሃሪያች መሳሪያ እንዳይሆን:በዚህም የራሱን የነጻነት ትግል እንዳያሰናክል:አድሃሪያች ወጥመድ ውስጥ ተወርውሮ እንዳይገባ እናስተምረዋለን::ይህንንም ስናደርግ የመደቦች ትግል የሚደረጅበትን ዘዴ ማፋጠናችን ነው::ይህን ስናደርግ ይህንን አቋም እንደሚቃወሙት ጓዶች ስለመደቦች ትግል አዋጅ መናገር ሳይሆን በትግል ለመደቦች ትግል መንገድ መጥረጋችን ነው::

ይህንን አቋማችንን የሚቃወሙ ጓዶች ፈጽሞ ያልተመለከቱት አንድ ነገር አለ::ኢትዮጵያን የሚያዩት 'ከነሱው' ተነስተው ነው::ሳይንሳዊ የሆነው የህብረተሰብ አርምጃ ህግ ለነሱ 'ተገለጠላቸዋልና ሰው ሁሉ የገባው መስሎአቸዋል::ለኢትዮጵያ አብዮት የጊዜውን ተግባር ሲወስኑ:መንገዳቸውን ሲቀይሱ መነሻ አድርገው የሚወስዱት የነሱን 'በቴዎሪ መብሰል' ደረጃ እንጂ የኢትዮጵያን ተጨባጭ ሁኔታ አይደለም:: እኛ ግን በማንኛውም ነገር መነሻ አድርገን የምንወስደው



የሃገሪቱን ተጨባጭ ሁኔታ ነው::የኢትዮጵያን አብዮት:የጊዜውን ተግባር:ስንወስን መንገዳችንን ስንቀይስ የምንነሳው ከኛ ሳይሆን ከኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ:ከህዝቡ የፖለቲካ ንቃት ደረጃ:ከትግሉ ... ወዘተ. እየተነሳን ነው::

ታዲያ ደግሞ የአንድ ህዝብ ፖለቲካዊ ህሊና የሚታነጸው ከመጽሀፍ የምናገኘውን 'ቲዎሪ' እንደዳዊት ስንደግምለት አይደለም:: የምንናገረው ሁሉ ሺህ ጊዜ እውነትም ቢሆን ህዝቡ የሚቀበለው የሚያየውን:በየእለቱ የሚያጋጥመውን:የሚጨበጥለትን እውነት ብቻ ነው::ከዚህ ተነስቶ ነው 'እኛ የምናንበለብለው ቲዎሪ'ከትምህርትና ከትግል በኋላ ሊገባው የሚችለው::

በአሁኑ የኢትዮጵያ ሁኔታ 'ህዝቡ በሙሉ ነው የተበደለው' የሚሉት አነጋገር እውነት ነው::ግን በቂ አይደለም:: የጊዜው ስርአት የኦሮሞው: የጉራጌው: የትግሬው: የኤርትራው: የአማራው ጠላት ነው ማለትም ሺህ ጊዜ እውነት ነው::ግን ይህም በቂ አይደለም::ይህ እውነት የመላውን የኢትዮጵያን ተበዝባዥ ተቀባይነት አግኝቶ የማይበገር የለውጥ ሞተር የሚሆነው አማራው ተራማጅ የተጨቆኑ ብሄሮችን ትግል በመደገፍ ለትግላቸው አንድነቱን ሲገልጽ:የብሄሮችን እኩልነት በማስተማር አድሃሪው ስርአት የሚነዛውን ትምክህተኛ ብሄራዊ ስሜት በድፍረት ሲዋጋ:ከዚህ ሁሉ በላይ ደግሞ አማራው ህዝብ በበኩሉ ተነስቶ ይህን ስርአት ለመደምሰስ ከወንድሞቹ ጋር በትግል አብሮ መፈተኑ ሲታይ ነው::

ይህ ደግሞ ጊዜ የሚወስድ ጉዳይ ነው::ስለዚህም ትግሉ ከመጀመሪያው ቀለጥ ያለ የመደብ መልኩን ይይዛል ብለን

ቀቤ እንጉቶልን አንልም፡፡በትእግስትና በርጋታ ትክክለኛውን ፖለቲካ እየተከተሉ የመደብ ትግሉን በማገዝ ፈንታ በአንድ ጊዜ ፊሽካ በመንፋት 'በኢትዮጵያ ያለህ ተበዝባዥ፡በኢትዮጵያ ያለህ በዝባዥ በወዲያ' በሉ ለማበለፍ መሞከር ጨርሶ የዋህነት ብቻ ሳይሆን የጊዜውን ዋና ተግባር በመሳት ቀስ በቀስ የመደብ መልኩን የሚይዘውን ትግል ማደናቀፍም ይሆናል፡፡

በበኩላችን የጠቀስነውን ትክክለኛ ፖለቲካ/በትምክህተኛ ብሄራዊ ስሜት ሳንወናበድ/ በተከተልንና የትግሉን እርምጃ በሚገባ ካገዝነው ትግሉ እየተፋፋመ ሲሄድ የአማራው፡የትግሬው፡የኤርትራው፡የጉራጌው፡የወላሞው ... ተጋዳይ ህዝብ በትግሉ ውስጥ እየተፈላለገ አንድነትን ያጠነክራል የሚል የጠበቀ እምነት አለን፡፡ስለዚህ የብሄራዊ ንቀና ቂሞችን እንገፈራቸውም፡፡አናድበሰብሳቸውም፡፡ተራማጆች ሁሉ በተደራጀ ሃይላችን ተቀብለንና አፋፍመን በተቻለ ፍጥነት የመደብ መልካቸውን እንዲይዙ ማድረግ የማናወላውልበት አደራችን ነው፡፡

## የትግል አንድነት

በኢትዮጵያ የሚገኙ ተበዝባዦች በሙሉ የጋራ ጠላታቸውን ፊውዳሊዝምንና ኢምፔሪያሊዝምን ለመደምሰስ የግድ መተጋገዝና መረዳዳት አለባቸው፡፡የትግል አንድነት የግድ ያስፈልጋል፡፡ይህ ትክክለኛ አቋም ነው፡፡በበኩላችን ባና ድጋፍ እንታገልለታለን፡፡ይህ የትግል አንድነት ሊገኝ የሚችለው ለብዙ ዘመናት በአድሃሪያን የተነዛው የመናናቅ፡የጥላቻ፡



ያለመግባባት መንፈስ ከሰፊው ህዝብ ህሊና ሲወገዱ ብቻ ነው፡፡

እዚህም ላይ እንግዲህ ከላይም እንዳልነው የትግል አንድነት በምንልበት ጊዜ ከወቅቱ ከሃገሪቱ ተጨባጭ ሁኔታ ተለይቶ ሰማይ ላይ የሚያንዣብብ የቲዎሪ መልስ ብቻውን እምብዛም አይረዳንም፡፡የረዥም ጊዜ አላማና ተግባር ከጊዜው አላማና ተግባር ተደባልቆ እንዳይቀርብና ለእርምጃ እንቅፋት እንዳይሆን አጥብቆ መጠንቀቅ ያስፈልጋል፡፡

መጀመሪያ ነገር፡በአንድ አገር ውስጥ/በተለይ የተለያዩ ብሄሮች ሲኖሩ/ የሚደረገው ጭቆና መልኩም ሆነ ከየብሄሩ የሚያስከትለው መልስ በሺህ በሚቆጠሩ የተለያዩ ነገሮች የሚወሰን ጉዳይ ነው፡፡ስለዚህም በሃገሪቱ በሙሉ የሚደረገው ጭቆናና የሚከተለውም የፖለቲካ ንቃት በጣም የተለያየና የተበላለጠ መልክ አለው፡፡ስለዚህ አሁንም ትግሉ ሲጀምር ከዳር እስከዳር በአንዴ 'ተነሳ' እየተባለ አይደለም፡፡ትግሉ አንድ ቦታ ይፋፋማል፡፡ሌላው ጋር ይዳፈናል፡፡አንዱ ጋር ይጣደፋል፡፡ሌላው ጋር ያዘግማል፡፡አንዱ ጋር በጣም ተራምዷል፡፡ሌላው ጋር ገና አልታለመም፡፡በተለያዩ ሁኔታዎች ተጨቁነው ከሚገኙ ተበዝባዦች ጋር ተቀላቅለን ትግሉ የምናስብ ሰዎች ይህን ቀላል እውነት ካልተቀበልንና የምትሰጠንንም ትምህርት ካልቀሰምን እንዲሁ 'የመደብ ትግል' እያልን ስንጠባበቅ ይመሽብናል፡፡

የተግባራችን ሁሉ መነሻ ትግሉ በተበታተነ መልክ መነሳቱን ያምናል፡፡መቸም የኛን አቋም የሚቃወሙ ጓደኞች ይህን የሚስቱት አይመስለንም፡፡ያቃታቸው የሚመስለን ከዚህ

መሰረታዊ እውነት የሚገኘውን ትምህርት መቀሰምና የሚከተለውን ጊዜያዊ ተግባር በሚገባ መወሰን ነው::

ለትግል አንድነት በዚህ ሁኔታ ምን እናድርግ:: ተግባራችንስ ምንድን ነው ሲባል እኛ ወደኋላ የቀረው ይፍጠን እንላለን:: የኛን አቋም የማይቀበሉ ደግሞ አፍ አውጥተው ባይናገሩም የፈጠነው ቀስ ይበል ይላሉ::

ገና 'ብሄራዊ ንቅናቄ' ሲባል ጉራጌውን ለመምዘዝ የሚቃጣው ትምክህተኛው አጉል ተራማጅ አቋም ስለዚህ ትግል አንድነት ሲያወራ የሚታየው ያው የፈረደበት 'የንኡስ ከበርቴ ናሽናሊስትስ' እንቅፋትነት ብቻ ነው:: ትክክለኛውን አቋማችንን የሚቃወሙት ኃይሎች ባወጡት ውሳኔ ላይ እንዲህ ይላሉ:—

'የኢትዮጵያ ተራማጆች በሙሉ በንኡስ ከበርቴ ናሽናሊስትስ ድንፋታ ባይወናበዱ ... የብሄሮችና የየክፍለሀገራት ሰፊ ህዝብ አንድነት መጠበቅና ልዩ ፖለቲካ/ሴክቴሪያን/ የሚከተለውንና አፈንጋጩን መታገል አለባቸው:: ... ብዙ ብሄሮችንና ብዙ ክፍለሀገሮችን ጠቅልሎ የሚይዝ አብዮታዊ ድርጅት እንዲቋቋም መጣር አለባቸው::' ተራማጅ ነኝ ባሉ በነዚህ በተጠቀሱት አላማዎች የማይስማማ የለም::

ነገር ግን ለዚህ አላማ ሲባል ከማን ጋር ነው በቀዳሚያ የምንታገለው:: ያልተነሳውን እንቀስቅሰው ወይስ የተነሳውን እንኮንነው:: በተበዘባዦች መሀከል አንድነት እንዲፈጠር: የተበዘባዦች አብዮታዊ የትግል አንድነት እንዲቋቋም /ከብሄሩ የአንድነት ጠላት ባይጠፋም/ ዛሬ ዋናው እንቅፋት የትኛው ነው::



የእነዚህ ኃይሎች አቋም ሃይለኛውን ጊዜያዊ አቋም እየሸሸ ደካማውን ጊዜያዊ ወዳጅ ሲያባርር እዚህም ላይ በትምክህተኛነትና 'በአፖርቹኒስትነት' ይጋለጣል::

እነዚህ ኃይሎች ነገሩን ሁሉ አደበላልቀውት ቁጭ ብለዋል:: ለምንፈልገው የትግል አንድነት ዋናው ጊዜያዊ እንቅፋት የተጠቀሱት ብሄሮች መነሳት ሳይሆን የአማራው ተደራጅቶ አለመነሳት መሆኑን መገንዘብ አቅቷቸዋል:: ከሁሉ ይበልጥ ደግሞ አማራው ህዝብ ለገዛ ነጻነቱ ከመነሳት አልፎ በማመረዝበት ትምክህተኛ ብሄራዊ ስሜት ለአድሃሪያን መሳሪያ ሊሆን እንደሚችል አይታያቸውም:: በዚህም ስሜት፡ እስከተያዘ ድረስ አማራው ቢነሳም ከወንዶቹ ጋር ሳይሆን በወንዶቹ ላይ መሆኑን ፈጽሞ ሊያዩት አልቻሉም:: ይህንን ሁሉ አደጋ ማየት ስላልቻሉ ደግሞ ዛሬ ለትግል አንድነት የሚደረገው ትንንቅ 'የንኡስ ከበርቴ ናሽናሊስቶች' ካዘሉት ንኡስ አደጋ ጋር ብቻ መስሏቸዋል:: እንዲያውም ዋናው ትግል ከሱ ይበልጥ የተበዝባዦች ሁሉ ጠላት ከሆነው ከአድሃሪው ትምክህተኛ ስሜት ጋር መሆኑን መገንዘብ አልሆነላቸውም::

እንደዚህ አይነቱ ቀዳሚያን ማደበላለቅ እነዚህን ኃይሎች ፈጽሞ ያሚጸለያቸው ምልክታቸው ነው:: ከላይ በመደብ ትግል ያየነውን ዝቅ ብለን ደግሞ 'ስለመገንጠል' መብትና 'ስለአንድነት መብት' ስናወራ ደግሞ የባሰውን ዝብርቅርቅ አውጥተውት እናገኛቸዋለን::

በበኩላችን ምንም ጊዜ ጥረታችን የትግል አንድነት እንዲመሰረት ነው:: ከአሁኑ የምንታገለው ለዚሁ አላማ ነው::

ነገር ግን ይህ የትግል አንድነት ከመጀመሪያው ካልተመሰረተ አያልን ድርቅ በማለት የብሄሮችን ንቅናቄያች በየሰበቡ ለማንቋሸሽ አንሞክርም:: ዋናው ተፈላጊው የትግል አንድነት፡ ተበዝባዦች በሙሉ በአንድነት ተባስረው በዝባዦችን የሚታገሉበት አንድነት ነው:: ስለዚህ ትግሉ ቀስ በቀስ ከየብሄሩ በተውጣጡ ተራማጆች የተቀናበረና የተደራጀ ጥረት የመደብ ትግሉን እየያዘ ሲሄድ የሚዳብር አንድነት ነው:: ስለዚህ የኛ ተግባር በየወቅቱ የሚጣለብንን አደራ በሚገባ በመረዳትና ተግባራችንንበሚገባ በመፈጸም ይህ ቋሚ የትግል አንድነት የሚመሰረትበትን መንገድ ለማስናዳትና የሚመሰረትበትን ጊዜ ለማፋጠን ተግቶ መታገል ነው::

ለዚህ አቋማችን ደግሞ ታሪክ በኛ በኩል ነው:: ታሪክ ደጋግሞ እንዳሳየው/ዛሬም እንደምናየው/ በዝባዦች ጥቅማቸውን ለመጠበቅ፡ከህዝብ ቁጣ ለመዳን፡እንኳን ኩታ ገጠም ሆነው ይቅርና ውቅያኖስም አያቋረጡ ቢሆን የመደብ አንድነታቸውን ይመሰርታሉ::

በኢትዮጵያ የሚደረገው ትግል እየተፋፋመና እያደገ ሲሄድ የየብሄሩ ተበዝባዥ-ህዝብ ወላዋይ መሪዎችን እየጣሰ በማለፍ ዘላቂና ህዝባዊ በሆኑ ግንባር ቀደም ሃይሎች ይተካቸዋል:: በዚህም ጊዜ ከየብሄሩ የተውጣጡትን ወላዋዮችና አድሃሪዎች በያለበት የሚተረፈረፉባቸውንና የሚቀድማቸውን የህዝቡን ቅስም ለመስበርና ትግሉን ለመግታት ታርቀው እንደሚተባበሩ ሳይታለም የተፈታ ጉዳይ ነው:: የዘመዱ ጥል የስጋ ትል ይባላል:: የበዝባዥ ጥል የስጋ ትል በንለውም ያው ነው::



በትግሉ ውስጥ የበዝባዦቹ ወገን እየተሳሰረና እየተባበረ ሲሄድ የተበዝባዦም ወገን አንድነቱን እንደበረት እያጠነከረ ወደፊት መግፋት አለበት:: ለአድሃሪዎች አመጽ አጸፋው አብዮታዊ የህዝብ አመፅ ነው:: ለአድሃሪዎች ጸረህዝብ አንድነት አጸፋው አብዮታዊ የህዝብ አንድነት ነው::

ጥያቄው ለዚህ ለተበዝባዦች የትግል አንድነት ዛሬ ተግባራችን ምንድን ነው የሚለው ነው:: በኛና የኛን የብሄራዊ ጉዳይ አቋም በሚቃወሙ ጓዶች መሀከል በዚህ ጥያቄ ላይ ያለውን ልዩነት ከፍ ብለን አይተነዋል::

ለዚህ አንድነት መንገድ መጥረግ ማለት ከዛሬው በኢትዮጵያ ተበዝባዦች መሀከል ለዘመናት ሲነዛ ቆይቶ መንፈሳቸውን የመረዘውን ጥላቻና አለመግባባት ማስወገድ ነው:: ተራማጆች ሁሉ ለዚህ መግባባት መስራት አለባቸው:: ለዚህም በአንድ በጠበቀ አብዮታዊ ድርጅት ውስጥ ተሰለፈው የሰፊውን ህዝብ አንድነት ለማጠንከር የተቀናበረ ፖለቲካ ማካሄድ አለባቸው::

ይህም ማለት ከሁሉ አስቀድሞ በትግሉ ውስጥ የአማራው ተራማጅ የሌሎችን ብሄሮች ትግል መደገፍ ከዚያም የትግላቸውን ፍች ለአማራው ህዝብ ባይታከት ማስረዳትና በበዝባዦች የሚነዛውን ትምክህተኛ ብሄራዊ ስሜት መዋጋት ተግባሩ ነው:: እንደዚሁም ደግሞ የአማራው ሰፊ ህዝብ ተነስቶ ከወንድሞቹ እንዲደባለቅ መጣር አለበት:: በዚህ ጊዜ ብቻ ነው "አማራም ተበዝባዥ አለ" የሚለው የሚኖረውና የሰፊውን ህዝብ ተቀባይነት የሚያገኘው:: እንደዚሁ ነው ለትግል አንድ

ነት አንድ ታላቅ መሰረት የሚጣለው::ለዚህም ዛሬ ተቀዳሚነት የሚሰጠው ተግባር አድሃሪውን ትምክህተኛ ብሄራዊ ሰሚትን እየተዋጉ ለብሄሮች ሙሉ እኩልነት መታገል ነው::

በሌላ በኩል ደግሞ በትግሉ ውስጥ የተጨቆኙ ብሄሮች ተራማጆች የተለየ አደራ አለባቸው::በጠቅላላው ህዝቡ ጭቆናን እንዲቋቋም ማነሳሳት:ማደራጀት:በብሄሩ ውስጥ የመደብ ትግልን እያፋፋሙ:በዝባዦችን ማጋለጥ:የአማራው ህዝብ ራሱ የተጨቆነ ህዝብ መሆኑን ለተበዝባዦች ሁሉ ማስተማር:'ለራሴ በቻ' እያለ አንድነትን የሚሸሸውን ጠባብ ብሄራዊ ሰሚት ሳይታክቱ መዋጋትአለባቸው:: የብሄሩን ትግል ያነሳሱት ከበርቴያችም ሆኑ ንኡስ ከበርቴያች በተቻለ ፍጥነት እየታለፉ እንዲሄዱና የህዝብ ትግል እንዲፋፋም ወላዋዬቹን ሳይታክቱ ማጋለጥ አለባቸው::ይህ ትግላቸው ፍሬ ሲሰጥ 'ኤርትራዊ በዝባዥ አለ':'ኦሮሞ በዝባዥ አለ' የሚለው እውነት ተጨባጭ ማመሳከሪያ ያገኛል::በሰፊው ህዝብ መንፈስ ይቀረጻል::ለትግል አንድነት ሌላ ታላቅ መሰረት ተጣለ ማለት ነው::ዛሬ የሰፈነው አድሃሪው ትምክህተኛ ብሄራዊ ሰሚት ተዳክሞ እኩልነት እየዳበረ ሲሄድ:ተራማጆች በሙሉ ተቀዳሚነት የሚሰጡት ተግባር ጠባብ ብሄራዊ ሰሚትን እየተዋጉ ለብሄሮች የትግል አንድነትና መፈቃቀድ መታገል ይሆናል::

## የብሄሮች የገዛ–እድላቸውን መወሰን መብት

ማህበራችን በዚህ በኩል የተቀናበረ ጥንድ ፖለቲካ ይከተላል::በአንድ በኩል ብሄሮች የገዛ እድላቸውን ለመወሰን ያላቸውን መብት እስከመገንጠልም ድረስ እንዲታወቅ ይ



ታገላል::ይህ አቋማችን ለብሄሮች ሁሉ ሙሉ እኩልነት የምናደርገው ትግል አካል ነው::በሌላ በኩል ደግሞ የነገደቶ ኢትዮጵያ ብዙ ብሄሮችን በማፈቃቀድ አቀፉ የያዘች ዲሞክራቲክ አገር እንድትሆን ይታገላል::ይህ አቋማችን ደግሞ ለሰፊው ህዝብ አንድነት የምናደርገው ትግል አካል ነው::

እንግዲህ ይህ ሲሆን በጣም የምንጠነቀቅበት አንድ ጉዳይ አለ:: የህዝቦችን እኩልነት መጠየቅ: የህዝቦችን አንድነት መጠየቅ 'በደፈናው' ምንም ተራማጅ አይደለም::እነዚህን አላማዎች አድሃሪዎች እንኳን እራሳቸው እናምንባቸዋለን ይላሉ::በአንድ በኩል 'ብሄሮች የገዛ እድላቸውን ለመወሰን:መነጠልን የሚጨምር:መብት' በሌላ በኩል ደግሞ 'ተፈቃቀደው በአንድነት ለመኖር' ያላቸውን መብት ከተቀበሉ በኋላ ተራማጆች ሁሉ ይህ ጥንድ ፖለቲካ የትግላቸው መሳሪያ እንዲሆን እንጂ እርስ በእርሱ እየተጣፋ እንዳያደናቅፋቸው መጠንቀቅ አለባቸው::አለበለዚያ እንደአድሃሪው:እንደ ትምክህተኛው:እንደጠባብ ናሽናሊስቶች በቃላት መጫወትና አይን አውጥቶ ማጭበርበር ይሆናል::

ለተራማጆች ይህ አቋም ተገበበበሰ በጅምላ የሚወረወር አቋም ሊሆን አይችልም::ነፍስ እንዲዘራበት ከተፈለገ በሁለት አቅጣጫ የተጣራ መልክ እንዲሰጠው ያስፈልጋል::

አንደኛ ትክክለኛውአቋም ለየብሄሩ ግለሰብ ተራማጅ በመልኩ በመልኩ የተለየ ተቀዳሚ ተግባሩን ሊያስታውቀው ይገባል::ይህ 'የአገሩን በርደ በአገሩ በሬ' እንደሚባለው መሆኑ ነው::ሁለተኛ ደግሞ ትክክለኛው አቋም ለአንድ ተራ

ማጅ ድርጅት በወቅት በወቅቱ እየለየ የጊዜውን ተቀዳሚና አጣዳፊ ተግባር ሊያመለክተው ይገባል::

እናብራራ::ትክክለኛው አቋም ለየብሄሩ ተራማጅ በመስክ በመስኩ የተለየ ተቀዳሚ ተግባሩን ሊያስታውቀው ይገባል አለን::ይህም ማለት በዛሬው ወቅት አማራው ተራማጅ ለአማራው ህዝብ የብሄሮችን እኩልነትና ብሄሮች የገዛ እድላቸውን ለመወሰን መገንጠልን የሚጨምር መብት እንዳላቸው ሊያስተምረው ይገባል::አማራው ተራማጅ 'የመገንጠል መብት' እንዲታወቅ መታገል አለበት::የተጨቋኙ ብሄር ተራማጅ ደግሞ በብሄሩ ውስጥ ያሉትን በዝባዦች ማጋለጥ:ከአማራው ህዝብ ጋር ያለውን አንድነት ለማጠንከር:በጠቅላላው 'የአንድነት መብት' ከሰራ ላይ እንዲውል መታገል አለበት::

ተግባሩ እንደዚህ በየመስኩ ካልተከፈለ ጠቅላላ ዝብርቅርቅ ይሆናል::መጀመሪያ ነገር ብዙ አለመደማመጥን ያስከትላል::ለኤርትራው ህዝብ አማራው ተራማጅ ሄዶ 'ስለአንድነት' ቢሰብከለት አያምርበትም::ኤርትራው ተራማጅ ለአማራው ሄዶ 'ስለመገንጠል መብት' ቢያወራው አይደማመጥም::አለመግባባት:ጥላቻ:አለመተማመን አለ የሚባለው አክ ለወዛ አይደለም::

ግን ደግሞ የባሰ አለ::ተግባሩ በየመስኩ ካልተከፈለ አቋሙ ለአጭበርባሪው 'ተራማጅ' ትልቅ የማጭበርበሪያ በር ይከፍትለታል::ይህ ደግሞ እስካሁን የታየ ነው::በአንድ በኩል ውሸቱን ለዚህ ጥንድ ፖለቲካ እታገላለሁ እያለ ከአድሃሪው ትምክህተኛ ስሜት ያልተላቀቀው አንዱ ተራማጅ



አለ::ይህ 'ተራማጅ' የመገንጠልን መብት ለስሙ ቢቀበልም በንርጆንጓውና በማስተማር ጥረቱ ሁሉ አጥብቆ የሚዘው 'ለአንድነት' የሚደረገውን ትግል ነው::ስለዚህ ለአማራው ህዝብ የሚያስፈልገው ትምህርት አይደርሰውም ማለት ነው::በወዲያ በኩል ደግሞ 'አለሁ' የሚለው የተጨቋኙ ብሄር 'ተራማጅ' ለአንድነት መብት ለይስሙላ ቢታገልም በንርጆንጓውና በማስተማር ጥረቱ ሁሉ አጥብቆ የሚይዘው በጠባቡ ብሄራዊ ስሜት የተከለውን 'የመገንጠል መብቱን' ከግቡ ለማድረስ ነው::ለተጨቋኙ ብሄር ህዝብም የሚያስፈልገው አልደረሰውም ማለት ነው::በመሀከል ማገናቸውም የተራማጅ ግዴታቸውን አልፈጸሙም::የጋራ ትግላቸውንም ባንዥ አልተራመደም::

ሁለተኛ ደግሞ ትክክለኛው አቋም ለተራማጆች ንቅናቄ በወቅት በወቅቱ እየለየ ተቀዳሚና አጣዳፊ ተግባሩን ማመልከት አለበት::ይህም ማለት ይህን ጥንድ ፖለቲካ በጠቅላላው ካወጁ በኋላ:የረዥም ጊዜ አላማውን በዚህ መልክ ከቀየሱ በኋላ:እንደጊዜው እንደአካባቢው:እንደትግሉ ደረጃ በመመራት ታክቲክን መቀየስ ያስፈልጋል::'ብሄሮች የገዛ እድላቸውን ለመወሰን ያላቸው መገንጠልንም የሚጨምር መብት' እንዲታወቅ እንታገላለን::'በመፈቃቀድ አንድነት እንዲመሰረት' እንታገላለን ቢባልም ማህበሩ ለሁለቱም መብቶች ሁል ጊዜ በእኩል ሃይል መታገል አይችልም::ለሁለቱም መብቶች ቢታገልም በትግሉ ውስጥ እንደሁኔታው እያየ አንዱ ሳንዱ:አንዱ ለሌላው ቀዳሚያ መስጠት አለበት::አለበለዚያ ያው እላይ ያየነው ይሆናል::ይጣፋል::ምናልባትም የአድሃሪ ያቸ

ና የአጉል ተራማጆች መሰሪያነት ከመሆን ቢያመልጥ እንኳን ሽፍንፍንና ተለካሻ አቋም ይሆናል፡፡ለትግል አይመችም፡፡

ለዘላቂ አላማችን የምንታገለው የአማራን ትምክህተኛ ብሄራዊ ስሜትንና ለራሱ ብቻ የሚለውን ጠባብ ብሄራዊ ስሜትን ነው፡፡ነገር ግን በአንድ በተወሰነ ጊዜ ሁለቱንም በአንድ አይን እመለከታለሁ የሚል አቋም ታክቲክና ስትራቴጂን ፈጽሞ የሚያደባልቅ፡የጊዜውን ዋና ጠላት በሚገባ የማይለይ፡ኢሱንም ለመዋጋት በይበልጥ የማያመዝን፡ዋናውን ትግል የሚሸሽ፡ወደ ነፈሰው የሚነፍስ አቋም ነው፡፡

ዋናና ዘላቂ አላማውን ወስኖ ማወጅ ብቻውን የተራማጆች ምልክት አይደለም፡፡በአንድ በተወሰነ ጊዜም የወቅቱን ዋና አላማ ከጠቅላላው ዘላቂ አላማ ለይቶ መያዝ፡የበሉ የጠሙትን እየታገሉ እሱን ከግቡ ለማድረስ መሞከር ያስፈልጋል፡፡ የትግሉን ዋና ሃይል ወደ ዋናው ጠላት መልሶ እሱን ማዳከም፡በዚያውም ራስን ማጠንከርና ለተከታዮቹ ጠላቶች በይበልጥ መሰናዳት፡እነሱንም በተራቸው በዚያው ቆራጥነትና አለማወላወል በመምታት አብዮትን ወደፊት ማራመድ የማንም ተራማጅ ቋሚ ተግባር ነው፡፡ሁሉንም በአንድ እዋጋለሁ የሚለው ተግደርዳሪ አቋም ግን አንዱንም በደንብ አይዋጋም፡፡

እንግዲህ ለኛ ጥያቄው ማን ይቅደም የሚለው ጥያቄ ነው፡፡ የጊዜው አጣዳፊ ተግባር ምንድን ነው፡፡ዛሬ በኢትዮጵያ የተናቁና በድርብርብ ጭቆና የተያዙ ብሄሮች ግፍ አስመርሯቸው እኩልነታቸውን ለማስከበር በተነሱበት ጊዜ፡አድሃሪው መንግስት ደግሞ 'በአንድነት' ስም ሊሰበስብ አመጹን



በሚያወርድባቸው ጊዜ <u>የጋራ ትግላችንን</u> ወደፊት የሚያራምደው ተቀዳሚ ተግባር የትኛው ነው፡፡በአድሃሪው መንግስት በገበና ጥይት በየእለቱ የሚረገጠውንና የሚሸረውን የብሄሮች እኩልነት ማወጅና እሱም እንዲታወቅ ሳይታክቱ መታገል ነው ወይስ በነዚሁ አጥፊ መሰሪያዎች ተደግፎና በአስከሪ አምነቶች ታጥር ለተያዘው 'አንድነት' መታገል፡፡ የምንፈልገው 'አንድነት' ዘላቂ አላማችን በመፈቃቀድና በእኩልነት ላይ የተመሰረተ 'የእኩዮች አንድነት' መሆኑ ሲታወቅ ተቀዳሚ ተግባራችን የትኛው ነው፡፡መሰረቱን መጣል ወይስ ልብስ የሚሆነውን ጣራና ግድግዳ እቀማለሁ ብሎ መግደርደር፡፡

በበኩላችን የምንመርጠው መንገድ ግልጽ ነው፡፡ዛሬ በኢትዮጵያ የብሄሮች ንቅናቄ በሚበዛበት ወቅት በፕሮፓጋንዳችንና በማስተማር ጥረታችን ሁሉ ሚሰበራችን ተቀዳሚነት የሚሰጠው ብሄሮች እኩልነታቸውንና የገዛ እድላቸውን ለመወሰን ያላቸው መብት እንዲታወቅላቸው መታገል ነው፡፡

የአማራው ህዝብ አድሃሪያኖች ለመግባት ከሚሞክሩት የበላይነት ስሜት መርዝ እንዲጠበቅ ለእኩልነት መታገል አለበን፡፡ግን ደግሞ ይሀ ብቻ አይደለም፡፡በዚያው አኳያ ደግሞ የተጨቆኑ ብሄሮች ህዝቦችም ቢሆኑ ለዘመናት በወረደባቸው አመጽና ጨለማ በራባቸው ያጡትን እምነትና ሰብአዊ ኩራታቸውን መልሰው እንዲጎናጸፉና በአብዮታዊ አመጽ ወደእኩልነት እንዲነሱ አመዛኙ ጉልበታችንን ለዚህ አላማ ልናውለው ይገባናል፡፡ዋናው የጊዜው አብዮታዊ ተግባር፡ዋናው የአንድነታችን መሰረት ይሄው ዛሬ ለእኩልነት የሚደረገው ትግል ብቻ ነው፡፡

ይህን አቋም የሚያወጡ ጓደኞች ነገሩ ሁሉ እንደሁ ሆኖ አይታያቸውም፡፡መጀመሪያ ነገር ለየብሄሩ ተራማጆች በሚገባ ተቀዳሚ ተግባርን አያከፋፍሉም፡፡ስለዚህ ውሳኔያቸውን ሲደረድሩ 'በኢትዮጵያ ያሉ ተራማጆች በሙሉ' እያሉ ነው የሚያወርዱት፡፡በዚህ ጉዳይ ላይ ለኢትዮጵያ ተከዝባኞች የሚሰጠው ትምህርትም ሆነ አቀራረቡ አንዱ ሊሆን እንደማይችል ከፍ ብለን ለማሳየት ሞክረናል፡፡እንመለስበትም፡፡

ከዚህ ይበልጥ የነዚህ ጓደኞች አቋም ፈጽሞ መስመር የሚስተውና አድሃሪያዊ ሲያገዝ የሚጋለጠው የጊዜውን ዋና ተግባር ለመቀየስ ሲነሱ ነው፡፡

'በዛሬው ወቅት በኢትዮጵያ ያሉ ተራማጆች ሁሉ በብሄሮች ጉዳይ ዋንኛ ተግባር አላቸው' ብለው ፈሀና ጀደምሩና ዝርዝር ውስጥ ይገባሉ፡፡ከፍ ብለን እንዳልነው እነዚህን ተግባሮች 'እንጌ ይሁን፡እንጌ ያንን' እያሉ አያከፋፍሉም፡፡እንነጋሁ ባሁኑ መሬት ለቀቀ በማይ ላይ የሚያንዣብብ አቋም ሆነ ማለት ነው፡፡ጉቶ የሚፈለው ከዚህ 'ዋንኛ ተግባር' ውስጥ 'ብሄሮች የገዛ አዱላቸውን ለመወሰን ያላቸው መገንጠልንም የሚጨምር መብት' እንዲታወቅ መደረግ ያለበት የአጅቴሽንና የፕሮፓጋንዳ ተግባር ሰፍ ቦል ተው አያነሱትም፡፡እርግጥ ስለዚህ መብት ያነሳሉ፡፡እንዲያውም 'የመገንጠልን መብት' እንድትታይም እንዳትታይም አድርገው አረፍተ ነገር መሀል ወሽቀ አድርገዋታል፡፡ለዚያውም ዋንኛ ተግባሮችን በሚዘረዝሩበት ቦታ አይደለም፡፡በዚህ ጉዳይ ላይ ዋርት ያለ፡ለትግል የሚመች አቋም የምንጠይቅ ሰዎች፡ከዚህም አለፈን ደግሞ ብሄሮች በዚህ በኩል ያላቸው መብት



እንዲታወቅ በፕሮፓጋንዳና በአጅቴሽን መታገል የጊዜው ዋና ተቀዳሚ ተግባር ነው ብለን ፍርጥ አድርገን የምንናገር ሰዎች በተራማጆች ስም የሚወጣ ውሳኔ ይህን መብት፡ይህን ጊዜያዊ ተግባር እንደዚህ ማድበስበሱ ያስደነግጠናል፡፡

እርግጥ ነው የጊዜው ዋንኛ ተግባሮች በሚዘረዝሩበት ለወጉ መጀመሪያ ላይ የሚጠቀሰው ተግባር 'የኢትዮጵያ ተራማጆች ሁሉ የጊዜውን የንጉስ ነገስቱን መንግስት ግዛት ወሰኖች መቀበል የለባቸውም' የሚለው ነው፡፡ይህ ተግባር መጀመሪያ ላይ የተወሰነው ለወጉ ነው ለምንድን ነው፡፡

ይህን ያልንበት ምክንያት መጀመሪያ ነገር ራሱ አቀራረቡ ቢፈሩ ቢቸሩ የስነዘረት መሆኑ ያስታውቃል፡፡'በወፍ ቋንቋ' ተናገረት እንጂ 'የጊዜውን መንግስት ወሰኖች አለመቀበል' ማለት በተጨራ አማርኛ ቢቀርብ የመገንጠልን መብት መቀበል ነው፡፡ሁለተኛ ነገር ደግሞ ልብ ያለው ሰው በነዚህ ጓደኞች 'የተግባ ዝጂ' ላይ የሚል ነገር አለ፡'የንጉስ ነገስቱን መንግስት ወሰኖች መቀበል የለብንም' በሚሉበት ጊዜ/ማለት የመገንጠልን መብት፡በዝወር ዋሬ መንገድ በሚቀበሉበት ጊዜ/ በዚህ በኩል ለሰፊው ህዝብ መስጠት ያለባቸው ትምህርት፡በለፕሮፓጋንዳና በለአጅቴሽን ሳንቲም አያነሱም፡፡በዚህ ጉዳይ ዋናው ተፈላጊው ነገር የነሱ ማወቅና አለማወቅ ሆነና ቀኙ አለ ማለት ነው፡፡ዝቀ ብለው 'እንዲነትን አጥብቀሁ ያዙ' ቢሉ በቻ ነው 'በፕሮፓጋንዳና በአጅቴሽን' ነጋሪት አያስመቱ አደባባ ብቀ የሚሉት፡፡እንግዲህ በነዚህ ጓደኞች አስተያየት በመገንጠል ጉዳይ አስጊው፡አስፈሪውና አጋፊው ፕሮፓጋንዳ መደረጉ ፈጽሞ ትርፍ ይከም

ነው ማለት ነው::እነዚህ ኃይሎች ሆን ብለው በየጊዜው ይህን መብት የሚያደበሰብሱትና በየጊዜው ዋናውን ትግል የሚሸሽ አቋም ስለሚከተሉ ዝቅ ብለን በኤርትራ መገንጠል ጉዳይም ይህን 'ሙያ በልብ ነው' የሚል ፖለቲካቸውን ይዘው እናገኛቸዋለን::

እንግዲህ እነዚህ ኃይሎች ለወጉ 'የመገንጠልን መብት' ከተራማጆች ተግባር እንደምንም ካወሩ በኋላ ለህዝብ በሚሰጠው ትምህርት ሲገቱም ሲያነሱ 'ወደሌላው ተግባር ያልፋሉ::ይህን "የተራማጆች ሁሉ ተግባር' ካወሩ በኋላ በዚህ ተራማጅ ትንፋሻቸው ብቻ አፈራርሰው ያጡትን የመሰሏቸውን 'አንድነት' መሰሰው ለመከብና ለመሰብሰብ 'በወጓ በኩል' ሃይልና ጉልበት ጨምረው ብቅ ይላሉ::ትንንታቸውን በጥና ለተከተለ ሁሉ ያስለመዱትን 'የንኡስ ከበርቴ ናሽናሊስቶች' አንቀፋትነት እዚህም ላይ ያመጡታል::ዝቅ ብለውም የነዚህን ጥንድ ተግባሮች ሌላ ዘት ሲደረድሩ 'የኢትዮጵያ ተራማጆች በሙሉ ... በንኡስ ከበርቴ ናሽናሊስቶች ባይወናበዱ በፕሮፓጋንዳቸውና በአጀቴሽናቸው የአስተዳደር ነጻነት /ናሽናል:ሪጅናል አቶኖሚን/ አጥብቀው መያዝ አለባቸው' ይሉናል::

'ስለመገንጠል መብት' ለህዝቡ ባንቱም ቢያስተምሩትም የጊዜው ዋና ተግባር አድርገው ወደሚወስዱት ወደ 'አንድነት መብት' ሲደርሱ ፕሮፓጋንዳና አጀቴሽኑን በሰፊው ይለቁታል::እንደዚህ አይነቱ አቋም ተራማጅ ንቅናቄያችን አጥብቆ መያዝ የሚገባውን ተግባር ፈጽሞ የሳተ ነው::እኩልነትና አንድነት አንጣጣም ብለው በእኩልነትና በነጻነት ሰዎ ብሄሮች



እየተነሱ ሲታገሉ:በአንድነት ስም ደግሞ እነሃይለስላሴ አድሃሪ አመጻቸውን በህዝቡ ላይ ሲያወርዱት እናያለን::በዚህ ጊዜ ተረግጦ ለተያዘው የብሄሮች እኩልነት በማድላት በፕሮፓጋንዳና በአጀቴሽን ሰፊ ትምህርት መዘርጋቱን ትተው በነሃይለስላሴ በገነባ ለሚታገዘው 'አንድነት' በይበልጥ ለመታገል የሚደረደር አቋም ሁሉ በህዝብ ትግል የሚያሳግጥና ወደአየለው እያደላ ትግልን የሚሸሽ አብሪ ተኛና አፖርቹኒስት አቋም ነው::

ከዚህ በላይ በጠቀሳሳው የምንከተለውን የፖለቲካችንን አቅጣጫ አሳይተናል::በዚህ ላይ አንዳንድ ማብራሪያዎችን መስጠት ተገቢ ይመስለናል::

ከሁሉ አስቀድሞ ይህን 'የመገንጠል መብት' በሚወቃቸውን 'አገር ሊበፋፍሉ ተነስተዋል' የሚል ማወናበጃ በያለበት ይበነዘርብናል::'ለአንድነት መብት' በመታገላችን ደግሞ አንዳንድ ጠባብ ብሄራዊ ስሜት ያጠቃቸው 'ብሄሮች የገዢ አድሎቸውን ለመወሰን ያላቸውን መብት' አያውቁም ሉናል::እዚህ ላይ በዚህ በኩል ሲጸፉ ብዙ ሰዎች የሚጠቅሱትን ምሳሌ መስጠት አንወዳለን::

አንድ ባልና ሚስት ተፋቅረው የመጋባት ብቻ ባሆን እንቻቻል ሲሉ ደግሞ የመፋታት መብታቸው እንዲታወቅላቸው ይገባል እንላለን::ይህ የሰው ልጅ ነጻነትና እኩልነት መብት የሚመለከት ጥብቅ ጉዳይ በመሆኑ መብቱ እንዲታወቅ:የጋብቻ ሁሉ መሰረትም እንዲሆን ከመታገል አናቆምም::ነገር ግን 'የመፋታት መብት' እንዲታወቅ በመታገላችን 'በራ

"ከመፍታት ለኛን ሳፋታት" ከሚሉት ወገን ልንቆጠር አይገባም።የትግር ጠሮች ብለን ልንወነጀል አንችልም።እንዲያውም ለዚህ መብት የምንታገለው ትግር በእኩልነት፣በመፈቃቀር፣በጋራ ወፈቃቀድ ላይ እንዲመሰረትና ጽኑ መሰረት እንዲኖረው በማሰብ ነው።

ከዚህ መሰረታዊ እምነታችን ስንነሳ በአንድ ባልና ሚስት ወፋታት ጉዳይ ምክር ብንጠየቅ እንደሁኔታው አይተን የሚሻቸውን ተመልክተን 'ይፋቱ' ወይም ደግሞ 'አይፋቱ' ልንል እንችላለን።የቤተሰቡን የጋራ ጥቅም፣የልጆችን ሁኔታ፣የጠቡን መክረር፣የመቻቻላቸውን እድል፣ሌሎችም መሰል ጉዳዮችን አውጥተን አውርደን ከመረመርን በኋላ ለባልና ለሚስቱ 'አትፋቱ' ብለን ልንመክር እንችላለን።ይህንን ስላደረግን ግን ባልና ሚስቱ ያላቸውን 'የመፋታት መብት' መርገጣችን አይደለም።እንደሁኔታው አይተን ደግሞ 'ተፋቱ' ልንል እንችላለን።ይህን ስላደረግን ደግሞ በየደረሰንበት 'የትግር ጠሮች' ልንባል አንችልም።

በሃገርም አንድነት ጉዳይ እንደዚሁ ነው።ተራማጆች በሙሉ ብሄሮች የገዛ እድላቸውን ለመወሰን መገንጠልንም የሚጨምር መብት እንዳላቸው እንዲታወቅ በጥብቅ መታገል አለባቸው።በሌላ በኩል ደግሞ ብሄሮች በመፈቃቀድና በእኩልነት የጠበቀ አንድነት እንዲመሰርቱ መታገል አለባቸው።'የመገንጠል መብት'ን ማወቃችን መከፋፈልን 'ሃይ ሃይ' አያልን ማገዛችን አይደለም።በሌላ በኩል ደግሞ በነገዴ ዲሞክራቲክ ኢትዮጵያ ብሄሮች ሁሉ በመፈቃቀድና በእኩልነት በአንድነት ይኖሩ ማለታችን ይህን መብ



ት መርገጣችን አይደለም።እንዲያውም በነገዴ ዲሞክራቲክ ኢትዮጵያ የምንታገልለት አንድነት በእኩልነት ላይ የተመሰረተና እያንዳንዱ ብሄር የገዛ እድሉን ለመወሰን ባለው መብት ተጠቅሞ 'ይሆነኛል' በሚለው መልክ ከሌሎች ብሄሮች ጋር የሚመሰርተው የእኩዮችና የፈቃደኞች አንድነት ነው።

ይህ ሁሉ ሆኖ አንዱ ብሄር ሊገነጠል ያለ እንደሆነስ።ለቻባሉ 'ኤርትራ ትገንጠል' ለሚለው አላማ መሰባቸው ምንድን ነው እንባል ይሆናል።

ይህ መቼስ እንደሁኔታው ለየተጠና የሚመለስ ጥያቄ ነው።አንዱ ብሔር ለመገንጠል መብት አለወይ ለሚለው ጥያቄ መልሳችን ሁሌ ጊዜ አወን መብት አለው ነው።አንዱ ብሄር 'ይገንጠል ወይ' ለሚለው ጥያቄ ደግሞ ከሁሉ አስቀድሞ መላሾቹ እኛ ሳንሆን የብሄሩ ተበዝባዦቹ ናቸው።እኛም በየጊዜው በዚህ ተጨባጭ ጥያቄ ላይ ሀሳባችንን ከመስጠትና ለሱም ከመታገል አናቋርጥም።

በኤርትራ ጉዳይ ከዚህ ጠቀሳሳ ፖለቲካችን የወጣ መስመር የለንም።የኤርትራ ህዝብ የገዛ እድሉን ለመወሰን ይታገላል።በዚህ ጊዜ ተራማጆች ትግሉን መደገፍና የገዛ እድሉን ለመወሰን መገንጠልንም የሚጨምር መብት እንዲታወቅለት በፕሮፓጋንዳና በአጅቴሽን አጥብቀው መታገል አለባቸው።

እዚህ ላይ መወሳት ያለበት አንድ ዋና ነገር አለ።ለተጨቆኑ ብሄሮች ተበዝባዥ ህዝብ የምንሰጠው ምክር ተደማጭነት የሚያገኘው አስቀድመን ብሄሮች የገዛ እድላቸውን ለመወሰን ያላቸው በምንም አይነት የማይደፈር መብት እንዲታ

ወቅ በሚገባ የታገልን እንደሆን ብቻ ነው። ይህን መብት በሚገባ ካወቅን በኋላ፡ እስከመጨረሻ ውጤቱ ተገንዝበን ከተቀበልን በኋላ፡ ጥንቀታችን ለዚህ በጦር ሃይል ታጥሮ ለተያዘው ለጊዜው የእስርቤት አንድነት እንዳይደለ ካሳየን በኋላ፡ ባጭሩ በፕሮፓጋንዳችን ሁሉ ይህ መብት እንዲታወቅ ከታገልን በኋላ ስለአንድነቱ ጉዳይ ምክራችንን በነበጥ ያምርበናል።

'ኢትዮጵያ ማለት እኔ ብቻ ነኝ' ብሎ ከከተመጨ ትምክህተኛ ብሄራዊ ስሜት ለአንዲት ሲክንድ እንኳን ጨርሶ ባለተቆራረጠ እንደበቱ፡ ለአንዲት ሲክንድ እንኳን ባለተፍታታ ሀሳናው ማንም ቢሆን ስለአንድነት ለመስበክ መብት የለውም። በዛሬው ወቅት አስቀደመን በፕሮፓጋንዳና በአጅቴሽን የመገንጠል መብት እንዲታወቅ ባንታገል 'ለአንድነት' እንታገላለን ብንል ከነሃይለስላሴ የምንለይበት ምንም አይነት ፈሊጥ የለም።

በዚህ ጉዳይ ላይ ከተቃዋሚያች ጓዶች ጋር ጥብቅ ልዩነት አለን። የኛ አቋም 'የኤርትራ ህዝቦች የራሳቸውን እድል ለመወሰንና ተነጥሎ ነጻ መንግስት እስከማቋቋም ድረስ ያላቸውን መብት' ያውቃል። ለዚህም የድጋፍ ድምጽ 'በየመጽሄቶች እንዲሰራጭ እንዲያደርግ' ከዚያም አልፎ 'የኤርትራና የኢትዮጵያ ህዝቦች የጋራ ጠላታቸውን ለመደምሰስ በሚያደርጉት ትግል በተግባር ላይ ሊተባበሩ የሚችሉበትን ሁኔታ እንዲያጠና' ባሳለፋቸው ውሳኔዎች አሳስቦአል።

ትክክለኛው አቋም ይህ ነው። መጀመሪያ መብቱን ማወቅና ይህ መብትም እንዲታወቅ በፕሮፓጋንዳና በአጅቴሽን መ



ታገል። ከዚያ ለአንድነት መታገል። ይህን አቋም የሚቃወሙ ጓዶች ነገሩን ሁሉ የተገላቢጦሽ ነው የሚያዩት። ስለኤርትራ መገንጠል ሲያወሩ አስቀድሞ መደረግ ስላለበት የፕሮፓጋንዳና የአጅቴሽን ትግል ባንዴ አያነሱም። ራሳቸውም ቢሆኑ ይህን መብት 'ለመደገፍ ተስናድተው የሚገኙት' አስቀድመው የደረደሯቸው ከአሸዋ የሚበዙ ነጥቦች ተሟልተው ከተገኙ በኋላ ነው። በውሳኔያቸው ላይ የሚሉት እንደዚህ ነው፦

'በተከዘባዦች አሳሳቢነት መገንጠል ከተጠየቀ በኤርትራ ያለው ንቅናቄ ጸረፊውዳልና ጸረኢምፔሪያሊስት ሆኖ በተከዘባዦች አመራር ስር ከወጣ፡ ንቅናቄው ከቀረት የኢትዮጵያ ተከዘባዦች ጋር የትግል አንድነትን አስፈላጊነት ሙሉበሙሉ ካመነ፡ የመገንጠሉ ተግባር በጠቅላላው ለኤርትራም ሆነ ለኢትዮጵያ ሌላ ክፍለ ሀገሮች የመደብ ትግል የተመቸ ከሆነ ተራማጆች ሁሉ በክፍለ ሀገሩ ነጻ መንግስት ሲቋቋም ለመደገፍ ተስናድተው መገኘት አለባቸው።'

የነዚህ ጓዶች 'ተራማጅ ውሳኔ' ያዘላቸውን እርስበርስ የሚጋጩና የሚጣፉ ሀሳቦች አንባቢ ስራ የፈታ ለት ያስላስላቸው ከማለት በስተቀር በዚህ ጥናታችን ውስጥ ልንዘረዝራቸው አንችልም። ግን የነዚህ ጓዶች አፖርቹኒስት አቋም ምንጊዜም ከዋናው ትግል እንዴት ነጥሏቸው እንደሚቀር ለማሳየት እንጩዳለን። የመገንጠሉን መብት ለመደገፍ 'ተስናድተው የሚገኙት' ትግሉ በተከዘባዥ አመራር ስር ከወጣና በትግል አንድነት አስፈላጊነት ሙሉበሙሉ ካመነ በኋላ ነው ይሉናል። ይህም ማለት ትምክህተኛ በሚትም ሆነ 'እኔ ብቻ' የሚል ብሄራዊ ስሜት ተጸበመው በፊው ህዝብ የአንድነትን

ጽኑ መሰረት ከጣለና ትግሉ ከፍተኛ ደረጃ ከደረሰ በኋላ
ነው ማለት ነው:: ነገር ግን ጉዱ በበሄሮች መሀከል መተማ
መንና አንድነት ፃበር ትግሉ እዚህ ከፍተኛ ደረጃ እንዲደ
ርስ እነዚህ ጓዶች ዛሬ በፕሮፓጋንዳና በአጅቴሽን አስፈላ
ጊውን ጥረት አያደርጉም::ከዛሬው ትግል በወጉ የሉበትም
ማለት ነው:: ነገሩ::ትግሉ ከዚህ ጓዶች 'ከሚመኙት' ከፍተኛ
ደረጃ ከደረሰ በኋላ ደግሞ የመገንጠል ጥያቄ በመጣም ህዝ
ቡ አስቀድሞ ሌሎች ባደረጉት ፕሮፓጋንዳና አጅቴሽን የተሰ
ናዳበት ጉዳይ ነው ማለት ነው፡ስለዚህ ዛሬ አይፋጠው የ
ሚጠበቀት ጓዶች ነገ 'ተሰናድተው' ቢቀ ማለታቸው ምን ለ
መጨመር እንደሆነ እግዚአብሄር ብቻ ይወቀ:: የሆነ ሆኖ ከ
ነገውም ትግል በወጉ የሉበትም ማለት ነው::

በዚህ ጉዳይ ከመጨረሻችን በፊት እነዚህ ጓዶች እን
ኳ 'የሚረሱትን' የማስተማር ተግባር ዋናነት ለማስተማር
አንወዳለን:: የመገንጠል ጉዳይ ሲሆን በነሱ አስተያየት ዋ
ናው ተፈላጊ ጉዳይ 'ተራማጆች ተሰናድተው መገኘታቸው' ነው::
ግን እስ ዋናው ጥያቄ የነሱ መሰናዳት አለመሰናዳት አይደ
ለም::እና ተሰናድተን በሚሊዮን ለሚቆጠረው ህዝብ ማስተማ
ር አለብን::ይህን ተራማጅ ተግባራችንን በሚገባ ከፈጸምን
የመጣ በመጣ የምንፈልገው አንድነት ከተርምሱ መስጥ አይመ
ለስም:: ነገር ግን ይህን መብት ተቀብለን ሰፊው ህዝብም
እንዲቀበለው ካልታገልን በሄድንበት ብንሄድ የምንፈልገውን
አንድነት አይከመነው እናርፋለን::

እንዲት::ይህ መብት በሰፊው ህዝብ ሀሳና እንዲታነ
ጽ አስፈላጊውን ትግል ካደረግን የመጣ በመጣ የህዝቡ አን



ድነት አይሞትም::እንድ ብሄር በዚህ መብት ተጠቅሞ በቀድ
ሞው ግዛት ውስጥ ለመቀየት ቢፈቅድ፡ይህ አንድነት በመፈቃ
ቀድና በእንድነት ላይ የተመሰረተ ጽኑ አንድነት ነው::በ
ሌላው በኩል ደግሞ አድሃሪያቹ በያለበት ለጊዜው አይለው
ተቻቸሉ መናር ፈጸሞ አዳጋች ሲሆንና በሁለቱም ወገን በዚ
ህ ጉዳይ የተነሳ የመደቦች ትግል ፈጸሞ ቢታፈን ለተ
በዝባዦቹ ሁሉ እውነተኛ የነጻነት ትግል ቢባል ለጊዜውም
ቢሆን መለያየቱ ይሻላል::በዚህም ጊዜ ቢሆን ተራማጆች ይ
ህን መብት አውቀው እንዲታወቅም ታግለዋልና መለያየቱ በሰ
ፊው ህዝብ መሀከል ያለምንም መቃቃር ይፈጸማል::በሁለቱም
ወገን ተራማጆች የቻሉትን ያህል ተግባራቸውን ፈጸመዋልና
የመተባበርና የአንድነት መንፈስ ለጊዜው ቢዳፈንም ጨርሶ
ከመሞት ይድናል::

ነገር ግን ይህን መብት ካላወቅን /ወይም እንደተቀ
ዋሚያቹ ጓዶች 'ሞያ በልብ ነው' በማለት እና 'ተሰናድተ
ን'ህዝቡን የማሰናዳቱን ነገር ቸላ ካልን/ በየትም በኩል
ቢታይ ለሰፊው ህዝብ እውነተኛ አንድነት ምንም አለሰራንም
ማለት ነው:: ተጨቋኙ ብሄር እንደምንም ታግሉ ራሱን ነጻ
ቢያወጣ ይህን ነጻነቱን ነጥቆ የሚወስደው ከአድሃሪያቹ ብ
ቻ ሳይሆን ተራማጅ ነን እያሉ ትግላቸውን ካልደገፉት ሰያ
ቸና በትምክህተኛ ስሜት ተመርዝ ከበዝባዦች ተደርቦ ከወጋ
ው ሰፊ ህዝብም ጭምር ነው ማለት ነው::ይህም መለያየት
በሰፊው ህዝብ መሀከል ያለውን መቃቃር ያባብሰዋል እንጂ
በምንም አይነት የምንፈልገውን መግባባት አያስገኝም::በሌ
ላ በኩል ደግሞ የተጨቋኙ ብሄር ትግል ለጊዜው ተሸንፎ በ

ሄሩ ባለበት ግዛት ውስጥ እንደታሰረ ቢቆይ ጭቆናው የባሰ ውን በለሚቀጥል በሰፊው ህዝብ መሀከል ያለው ጠብና አለመግባባት ከመቼውም እየከረረ ይሄዳል::

## መደምደሚያ

ከላይ የጠቀስናቸው ልዩነቶች ተጠራቅመው እናገና ተቀዋሚያችን ኃይሎች በጠቅላላው በኢትዮጵያ አብዮት ሁለት የተለያዩ ታክቲኮችን እንዲከተሉ ያደርጓል::

የኛ አቋም ከትምክህተኛ ብሄራዊ ስሜትም ሆነ ከጠባብ ብሄራዊ ስሜት ፈጽሞ የተላቀቀ አቋም ነው::ዛሬ በኢትዮጵያ ካለው ተጨባጭ ሁኔታና ከዝቅተኛው የትግል ደረጃ ጋ ነባል::ዛሬ በኢትዮጵያ ውስጥ በልዩ ልዩ ብሄሮች መሀከል ጥላቻ አለመግባባት አለ::ይህም ቀራኔ በመጭው ጊዜ እየከረረ ሊሄድ እንደሚችል ያምናል::እንዲያውም ተራማጆች ሁሉ በየበኩላቸው ተግባራቸውን በሚገባ ካልፈጸሙ የኢትዮጵያ ተበዝባዦች በሙሉ ለነጻነት ትግላቸው ሊያውሉት የሚገባውን ሃይል አሰቃቂ በሆነ የእርስ በእርስ ትርምስ ሊያባክኑት የሚችሉበት አደጋ አለ ብለን እናምናለን::አቋማችን ከዚሁ እውነት ተነስቶ የከረረው ቀራኔ የሚለሳለስበትን፣ የመነመነው አለመግባባት የሚጸበርበትን ዘዴ ያመለክታል::አቋማችን የተያዘውን ትግል ወደፊት የሚያራምድ፣ የተጋፋዩን ሰፊ ህዝብ የትግል አንድነት የሚያረጋግጥ፣ ነገ ደግሞ በኢትዮጵያ የሚገኙ ብሄሮች በመግባባትና በአንድነት የሚኖሩበትን መንገድ የሚጠርግ አቋም ነው::ለዚህም ሁሉ በደፈናው የሚወረወር የቲወሪ መልስ ብቻውን ምንም ዋጋ እንደሌለው በመገን



ዘብ የጊዜውን ዋና ጠላት በማመልከት፣ የጊዜውን ዋና ተግባር በመወሰን ዛሬ በመላ ኢትዮጵያ ከሚደረገው ትግል በግንባር ቀደምነት የምንደባለቅበትን ዘዴ አበጥሮ ያሳያል::

ይህን አቋም የሚቃወሙት ኃይሎች ከአጠቃላይ ቲወሪ ወጥተው ኢትዮጵያን ማሰላሰሉ ፈጽሞ አልተሳካላቸውም::ለዚህ ነው ለምሳሌ 'ዋናው የመደቦች ትግል ነው' በሚል በደፈናው እውነት ከሆነ አነጋገር ተነስተው ዛሬ በኢትዮጵያ ብሄሮች መሀከል ያለውን ግጭት የሚንቁት::ለዚህ ነው ለምሳሌ ይህ ቀራኔ በጊዜ ካልተፈታ 'የመደቦች ትግል' መጨረሻው ለማይታይ ረጅም ጊዜ በእርስ በእርስ ትርምስ ተውጦ ሊቀር እንደሚችል እና የሚታየን አደጋ ለነሱ የማይታያቸው::

እነዚህ ኃይሎች ከአጠቃላዩ ተግባርና ከዘላቂ ግብ ማወጅ ወጥተው ዛሬው ባለው ሁኔታ የጊዜውን ዋና ተግባር በሚገባ መወሰን ተስኗቸዋል::ለዚህ ነው ለምሳሌ ለትግል አንድነትም ሆነ በጠቅላላው ለትግሉ እድገት በሚያደርጉት ጥረት ዋናውን እንቅፋት ረስተው 'ንኡስ ከበርቴ ናሽናሊስቶችን' እንደ ዋና ጠላት ቢያባዱቱ ከትምክህተኞችና 'ከኦፖርቹኒስቶች' ጋር ተደባልቀው የሚጋለጡት::ለዚህ ነው ለምሳሌ ለእኩልነትም ለአንድነትም እንዋጋለን ቢሉም የጊዜውን ዋና ግብ መወሰን አቅቷቸው ከሁለት ያጣ ጎመን የሆኑት::

የነዚህ ኃይሎች አቋም በየሰበቡ ብሄራዊ ንቅናቄያችን የሚንቅ፣ ትምክህተኛና ከአየለው ጋር የሚያይል፣ ትግልን የሚሸሽ 'ኦፖርቹኒስት' አቋም ነው::ስለዚህም በዛሬው ትግል ሰፊው ህዝብ፣ ንኡስ ከበርቴው፣ አገረ ወዳድ ከበርቴውና እ

ንዲያውም አንዳንዴ በሰበቱ ሁሉ ተግበሰበሰ ከሚዋጋበት ከዘቀተኛው የትግል ደረጃ በግንባር ቀደምነት ተደባልቀን ትግሉን ከፍ የምናደርግበትን ዘዴ አያበይም::ስለዚህም ከዳር ቆመው ከሚሽሟጠጥ በስተቀር ምንም የረባ የትግል መስመር ስለሌላቸው በውባኔያቸው መጨረሻ ወደማያመጡበት መደምደሚያ ይወስዱናል::'በመጨረሻም'ይሉናል እነዚህ ጋዶች ውባኔያቸው መደምደሚያ ላይ 'በመጨረሻም ተራማጅ ኢትዮጵያውያን በሙሉ ስለብሄሮች ጉዳይ . . . ጥናታቸውን መቀጠል አለባቸው'::

እናስ:: የኛ አቋም እርግጥ ይህንን ዝቅተኛ የትግል ደረጃ 'ኸለለ' እያለ አይቀበለውም:: ነገር ግን የሀገሪቱ ታሪካዊ ሁኔታ ያፈራው ነገር በመሆኑ ከስው ለመነሳት እንደ አንዱ ታሪካዊ የትግል ደረጃ አድርገን እንቀበለዋለን::ለኢትዮጵያ ሰፊ ህዝብ ነጻነት፡እኩልነት፡አንድነትና ብልጽግና የምንታገለው የግድ ከዚህ ዝቅተኛ ደረጃ በግንባር ቀደምነት ተዋህደን መሆኑ ይገባናል::ስለዚህ እነሱ 'ይጠና' በሚሉበት ጊዜ የኛ አቋም በኢትዮጵያ ካሉት ብሄራዊ ንቅናቄዎች ጋር ለጋራ ትግላችን የምንተባበርበትን ዘዴ ያሳያል::

የማህበራችን አቋም ትግል ለበሰበሰው ስርአት አደገኛነቱ፡ ለኢትዮጵያ ተበዝባዦች ደጋፊነቱ እዚሁ ላይ ነው::'እኩልነት':'አንድነት':'የመደብ ትግል'ወዘተ. እያለ መሪ ቃላትን ከመወርወር አልፎ ለነዚህ አላማዎች በጥብቅ ይታገላል::እንደዚሁ ነው ጭቁና በየመልኩ የሰፈረባት ኢትዮጵያ ሰፊ ህዝብ ከብረት የጠነከረ አንድነትን መስርቶ በአብዮታ



ዊ አመጽ በዝባዦችን እንደጎርፍ የሚያጥለቀልቃቸው::እንደዚሁ ነው የተደራጀው የህዝብ ትግል አገሪቱን የሚያጥባት:: ለዚሁ ነው አድሃሪያችን ሁሉ የማህበራችን አቋም እንደዚህ ያስቆጣቸው::

ንጋት አምዴ

ዋጋው፤ 1.50 ብር